# አዲስ ዘመን

ኢፕድ

ዓርብ

84ኛ ዓመት ቁጥር 073 ኅዳር 13 ቀን 2017 ዓ.ም ዋጋ 10:00 ብዕራችን ለኢትዮጵያ ህዳሴ ይተጋል!






ፎቶ ገባቦ ገብሬ

ዘለቀ ተመስገን (ዶ/ር)

# የሚኒስትሮች ምክር ቤት በተለያዩ ጉዳዮች ላይ ውሳኔ አሳለፈ

**በጋዜጣው ሪፖርተር**

<u>አዲስ አበባ</u>፡- የሚኒስትሮች ምክር ቤት በተለያዩ ሰባት ጉዳዮች ላይ ተወያይቶ ውሳኔ አሳልፏል፡፡

ምክር ቤቱ ትናንትና ባካሄደው 40ኛ መደበኛ ስብሰባው በቅድሚያ የተወያየው የመካከለኛ ዘመን (2017-2021) የማክሮ ኢኮኖሚና ፊስካል ማሕቀፍ ላይ ነው፡፡ ማሕቀፉ በሁለተኛው ምዕራፍ ሀገር በቀል ኢኮኖሚ ማሻሻያ የሚከናወኑ የማክሮ ኢኮኖሚ ማሻሻያዎችንና የመንግሥት የፊስካል ፖሊሲ ማሻሻያዎችን ተግባራዊ ለማድረግ እና ለ2017 የፌዴራል መንግሥት ተጨማሪ በጀትና የወጪ አሸፋፈን ማስተካከያ መነሻ ሆኖ የሚያገለግል ሲሆን በማክሮ ኢኮኖሚ ማሻሻያዎች ተቃኝቶና ተሻሽሎ የቀረበ መሆኑን ገልጿል፡፡ ምክር ቤቱም በማሕቀፉ ላይ


**የሚኒስትሮች ምክር... ወደ ገጽ 6 ዞሯል**


## በኢትዮጵያ ለጨርቃጨርቅ ግብዓቶች ተስማሚ ከሆነው መሬት 30 በመቶው ብቻ ለምቷል

**- በስድስት ዓመታት የጨርቃጨርቅ ወጪ ንግድ ገቢን አንድ ቢሊዮን ዶላር ለማድረስ ታቅዷል**

**ሄለን ወንድምነው**

<u>አዲስ አበባ</u>፡- የጨርቃጨርቅ ምርት ግብዓቶችን ለማምረት ምቹ ከሆነው መሬት 30 በመቶ ብቻ ማልማት የተቻለ መሆኑን የኢትዮጵያ ኢንቨስትመንት ኮሚሽን አስታወቀ። እ.ኤ.አ በ2030 የኢትዮጵያን የጨርቃጨርቅ ወጪ ንግድ ገቢን አንድ ቢሊዮን ዶላር ለማድረስ መታቀዱም ተመላክቷል።

የኢትዮጵያ ኢንቨስትመንት ኮሚሽን ከኪንግ ደም ግሩፕ ሆልዲንግ ጋር በመተባበር ያዘጋጁት "ዓለም አቀፍ የበፍታህ ጨርቃጨርቅ ፎረም 2024"ትናንት በአዲስ አበባ ተካሂዷል።

የኢትዮጵያ ኢንቨስትመንት ኮሚሽን ኮሚሽነር ዘለቀ ተመስገን (ዶ/ር) በወቅቱ ባደረጉት ንግግር እንደገለጹት፤ ኢትዮጵያ የጨርቃጨርቅ ምርት ግብዓቶችን ለማልማት ተስማሚ የሆነ ከአምስት ሚሊዮን ሄክታር በላይ መሬት አላት። ኢትዮጵያ ለጨርቃጨርቅ ምርት ግብዓቶች ተስማሚ ከሆነው ከአምስት


**በኢትዮጵያ ለጨርቃጨርቅ... ወደ ገጽ 6 ዞሯል**




ፎቶ ሀዲስ አብርሃ

ያይኔአበባ አስፋው

## ሙዝን በችርቻሮ ከመሸጥ ወደ ሙዝ ልማት የተሸጋገረችው ባለሀብት

**ሞገስ ፀጋዬ**

**ዜና ሐተታ**

ያይኔአበባ አስፋው ትባላለች፡፡ ትውልድና እድገቷ በአሁኑ ደቡብ ኢትዮጵያ ክልል በጋሞ ዞን በአርባ ምንጭ ከተማ ዙሪያ ወረዳ ነው፡፡ የተማረችው እስከ ስምንተኛ ክፍል ብቻ ነው፡፡ ቀደም ሲል ይህ ነው የሚባል ሥራ አልነበራትም፤ የዕለት ምግቧን ለመቻል ሌት ተቀን መንገድ ላይ በሳፋ ሙዝ በመያዝ ከአርባ ምንጭ ከተማ ለሚገቡና ለሚወጡ መንገደኞች ትሸጥ ነበር፡፡


**ሙዝን እያዞሩ ከመሸጥ... ወደ ገጽ 6 ዞሯል**


## "የስታርት አፕ" ምሰሶዎች

**ልጅዓለም ፍቅሬ**

**ዜና ትንታኔ**

"ስታርት አፕ" ኢትዮጵያ ለወጣቶች ሥራ ፈጠራ የተመቻቸ ከባቢን በመፍጠር ችግር ፈቺ የሥራ መስኮችን ለመክፈት ያለመ መሆኑን ጠቅላይ ሚኒስትር ዐቢይ አሕመድ (ዶ/ር) መጋቢት 2016 ዓ.ም መግለጻቸው ይታወሳል፡፡

ጠቅላይ ሚኒስትሩ ከለውጡ በፊት በሀገር አቀፍ ደረጃ ያሉ ስታርት አፖች ከ50 እንደማይበልጡ አውስተው፣ አሁን ላይ ከ900 በላይ ስታርት አፖች መኖራቸውን ነው የተናገሩት። ጠቅላይ ሚኒስትሩ አያይዘውም ወጣቶች በፈጠራ ሃሳብ የተሞሉ የሀገሪቱ አንቀሳቃሽ ሞተሮች መሆናቸውን በመቀበል ሀሳባቸውን ወደ ተግባር የሚለውጡበት የዘርፉ ፖሊሲ ድጋፍም እጅግ አስፈላጊ ነውም ብለዋል፡፡

በተለይ በቀደሙ ጊዜያት የነበሩ የአሠራር ማነቆዎች፣ የሚገጥሟቸውን የፋይናንስ እጥረት በማስወገድ በሥራ ሂደት የሚያገኙትን የውጭ ምንዛሪ መቶ በመቶ ለራሳቸው እንዲጠቀሙ እንዲሁም ምርቶቻቸውን በቀላሉ የሚሸጡበት የኢ-ኮሜርስ ዕድል ተመቻችቷል ማለታቸውም አይዘነጋም፡፡

በቅርቡም 16ኛው የዓለም አቀፍ የኢንተርፕርነርሺፕ ሳምንት በኢትዮጵያ ከኅዳር 9 ቀን 2017 ዓ.ም ጀምሮ





በተለያዩ ሁነቶች መካሄዱን ቀጥሏል፡፡ ይህ ጅማሮ ታዲያ በኢትዮጵያ በኢኮኖሚው፣ በቴክኖሎጂ እና በዲጂታሉ ዘርፍ ሁለንተናዊ እንዲሁም ዘላቂ ለውጥ እንደሚያመጣ የስታርት አፑ ዘርፍ ከፍተኛ ግምት ተሰጥቶታል፡፡

በቴክኖሎጂ ላይ የተመሠረተ ጀማሪ ሥራ ፈጣሪዎች ("ስታርት አፕ") በተለይ ለዲጂታል ኢኮኖሚ ግንባታ፣ ለቴክኖሎጂ ሽግግርና ለሥራ ዕድል ፈጠራ ከፍተኛ አስተዋፅዖ እንዳለው የዘርፉ ምሑራን ይገልጻሉ፡፡

በኢትዮጵያ ስታርት አፕን ለማሳደግና በዘርፉ የሚገኘው ተጠቃሚነት ለማረጋገጥ ምን መደረግ አለበት ሲል ኢፕድ የዘርፉ ተዋናዮችን አነጋግሯል፡፡

በሐረማያ ዩኒቨርሲቲ የምጣኔ ሀብት መምህርና ተመራማሪ ሀብታሙ ለገሠ እንደሚሉት፤ ስታርት አፕ የሥራ ባሕል የሚቀይር፣ አዲስ የኢኮኖሚ ዓውድ የሚፈጥር፣ በቀላሉ ማደግና መስፋፋት የሚችል፣


**"የስታርት አፕ"... ወደ ገጽ 6 ዞሯል**





# የሞተር ስፖርት አሶሴሽን በመንገድ ደኅንነት ዙሪያ እየሠራ ነው

**ዓለማየሁ ግዛው**

አዲስ አበባ ፡- ከስፖርቱ ጎን ለጎን በመንገድ ደኅንነት ላይ እየሠራ መሆኑን የኢትዮጵያ ሞተር ስፖርት አሶሴሽን አስታወቀ።

የአሶሴሽኑ ፕሬዚዳንት አቶ አዲስ ዓለማየሁ ለኢትዮጵያ ፕሬስ ድርጅት እንደገለፁት፣ ኢትዮጵያ ከፍተኛ የትራፊክ አደጋ ያለባት ሀገር በመሆኗ ፌዴሬሽኑ ከስፖርቱ በተጨማሪ በመንገድ ደኅንነት ላይ ለመሥራት አቅጣጫ አስቀምጦ እየሠራ ይገኛል።

እንደ ፕሬዚዳንቱ ገለፃ፣ አሶሴሽኑ በመንገድ ደኅንነትና አካባቢ ጥበቃ ላይ ለመሥራት የፓይለት ፕሮጀክቶችን ቀርፆ በጎሕ ካርትና በአውቶሞቲቭ ክለቦች ላይ ሥራውን ጀምሯል። በመንገድና ትራፊክ ደኅንነት ዙሪያ በተከናወኑ የፕሮጀክት ሥራዎችም አባሎችንና ደጋፊዎችን ማግኘት ተችሏል።

አሶሴሽኑ አውቶሞቲቭ ኢንጂነሪንግን በተመለከተ በሳምንት ቋሚ የቴሌቪዥን ፕሮግራም ቀርፆ በመንገድ ደኅንነት ላይ የማስተማር እቅድ ነድፏል። በእቅዱ መሠረትም የኢትዮጵያ ሞተር ስፖርት በኢትዮጵያ መንገድ ደኅንነት ላይ ዐሻራውን ለማሳረፍ እንቅስቃሴ መጀመሩን ፕሬዚዳንቱ ጠቁመዋል።

አሶሴሽኑ በዚህ ዓመት ስለ ስፖርቱ በዓለም አቀፍ ተሞክሮ ላይ ተመሥርቶ በሳምንት ቀጣይነት ባለው መልኩ በቴክኖሎጂ ሽግግር፣ በካይ ጋዝ፣ አካባቢ ጥበቃ እና በዋናነት ከመንገድ ደኅንነት ጋር የተያያዙ የግንዛቤ የማስጨበጫ ሥራዎችን ከዩኒቨርሲቲዎች ጋር በትብብር ይሠራል። በዚህም የኅብረተሰቡ ግንዛቤ እየተለወጠ እንደሚሄድ ፕሬዚዳንቱ ገልጸዋል።

በዓለም አቀፍ የሞተር ስፖርት ማኅበር እራስን ከአደጋ ተከላክሎ በማሽከርከር እና በመንገድ ደኅንነት ዙሪያ ሥልጠና መሰጠቱን ያስታወሱት ፕሬዚዳንቱ፣ ከመሰል ሥልጠናዎች የሚገኙ ተሞክሮዎችን ወደ ሀገር ውስጥ በማምጣት በመንገድና ትራፊክ ደኅንነት ዙሪያ ለመሥራት ጥረት እየተደረገ እንደሚገኝ ተናግረዋል። በአሶሴሽኑ እቅድ መሠረትም በዓመቱ ዓለም አቀፍ ልምዶችን ለመቅሰም ታስቦ ባለፈው ሁለት ወር ውስጥ ሲውዘርላንድ፣ ኬንያና ዱባይ ላይ ዓለም አቀፍ ተሞክሮዎችን እና የተለያዩ ሥልጠናዎችን ማግኘት እንደተቻለ አክለዋል።

የሞተር ስፖርት በባሕሪው በመኪና መንገዶች ላይ የሚካሄድና ለአደጋ ተጋላጭና አጋላጭ በመሆኑ ለወጣቶች እንዴት እራስን ከአደጋ ተከላክሎ ማሽከርከር እንደሚችሉ የጥንቃቄ ሥልጠና መስጠት ተችሏል። «በሞተር ስፖርት ዓለም አቀፍ ደረጃውን የጠበቀ ሥልጠና ስለሚሰጥ በዚህ ውስጥ አልፎ ወደ ውድድር የሚገባ አሽከርካሪ አደጋ የማድረሱ ዕድል ጠባብ ነው» የሚሉት ፕሬዚዳንቱ፣ ይህን ከስፖርቱ ውጪ ባሉ አሽከርካሪዎች መጠቀም ከተቻለ የተሽከርካሪ አደጋን በመቀነስ ረገድ ለውጥ ሊመጣ እንደሚችል እምነት እንዳላቸው ተናግረዋል።

ይህንንም ሲያብራሩ፣ አሽከርካሪዎች የሞተር ስፖርት ተወዳዳሪ እንኳን ባይሆኑ ሥልጠናውን ከወሰዱ መንገድ ላይ በሚያሽከረክሩበት ወቅት አደጋ የማድረስ ዕድላቸው ጠባብ እንደሚሆን ያስረዳሉ።

የሞተር ስፖርት ከቱሪዝም መዳረሻነት፣ ከትራፊክ አደጋ፣ ከተሽከርካሪ አማቂ ጋዞች፣ ከቴክኖሎጂ ሽግግርና ከሌሎች መንገዶች ጋር በተያያዘ ለሀገር ትልቅ አበርክቶ ያለው ስፖርት መሆኑን ፕሬዚዳንቱ ጠቁመው፣ ይህንን ለመጠቀም አሶሴሽኑ ከትራንስፖርት ሚኒስቴር ጋር በመንገድ ደኅንነት ላይ አብሮ ለመሥራት የሚያስችል የመግባቢያ ስምምነት ለመፈራረም ውይይት በማድረግ ግንዛቤ መፍጠሩን ገልጸዋል።

በተጨማሪ አሶሴሽኑ ከመንገድ ፈንድና መንገድ ደኅንነት ጋር አብሮ ለመሥራት ውይይት በማድረግ የመግባቢያ ሰነድ ተዘጋጅቶ ወደ ሥራ ለመግባት ዝግጅቱን አጠናቋል። ከእነዚህ አካላት ጋር በትብብር በትራፊክ አደጋና መንገድ ደኅንነት ዙሪያ በመሥራት ለውጥ ለማምጣት ብዙ እቅዶች እንዳሉትም ፕሬዚዳንቱ ተናግረዋል።

# በጋምቤላ ክልል ለበጋ መስኖ ልማት ዝግጅት እየተደረገ ነው

**ቃልኪዳን አሳዬ**

አዲስ አበባ፡- በዘንድሮው በጋ ወቅት የተለያዩ የሰብል፣ የአትክልትና ፍራፍሬ ምርቶችን በመስኖ ለማልማት በቂ ዝግጅት እያደረገ መሆኑን የጋምቤላ ክልል የእርሻና ተፈጥሮ ሀብት ልማት ቢሮ አስታወቀ።

የቢሮው ምክትል ኃላፊ አቶ ዳግም መላሽን ለኢፕድ እንደገለጹት፤ በ2016 ዓ.ም በበጋ መስኖ ልማት በአነስተኛ አርሶ አደሮች እርሻ ከ3ሺህ 300 በላይ ሄክታር መሬት ላይ የተለያዩ የሰብልና ሆርቲካልቸር ምርቶችን ማምረት ተችሏል። በተያዘው ዓመት የምርት ዘመን 5ሺህ 868 ሄክታር መሬት በተለያዩ የሰብል አይነቶች ለመሸፈን ታቅዶ እንቅስቃሴ እየተደረገ ነው።

ካለፈው ዓመት በተሻለ እቅዱ ከፍ ያለበት ምክንያት በግንባታ ላይ የነበሩና ነባሮቹ የመስኖ ልማት አውታሮች ተጠናክረው ወደ ሥራ የገቡበት መሆኑን አመልክተው፤ ከዚህም መካከከል ባሮ ፒንክዮ፣ ችቦኪር፣ ባዚየል፣ ኖር፣ ጊሎ ፖቻላ እና ኢሌይቾይ የመስኖ ልማት አውታሮች በዘንድሮ ዓመት ወደ ሥራ እንደሚገቡ አቶ ዳግም ጠቁመዋል።

ከአዳዲሶቹ በተጨማሪ የቦንጋ፣ የኩሚና ቶሊናቶካሊ



አቶ ዳግም መላሽን

ነባር የመስኖ ልማት አውታሮችን የማጠናከር ሥራ እንደሚሠራ ገልጸው፤ የተለያዩ የሰብል፣ የአትክልትና ፍራፍሬ ምርቶች ማለትም በቆሎ፣ ማሽላ፣ ስንዴ፣ ሩዝ፣ በርበሬ፣ ጥቅል ጎመን፣ ቲማቲም፣ ሽንኩርት፣ ሃብሀብና ሙዝ ላይ ትኩረት እንደሚደረግ አቶ ዳግም አውስተዋል።

ከሜካናይዜሽን ጋር ተያይዞ እያጋጠሙ የሚገኙ ተግዳሮቶች እንዳሉ የጠቀሱት ምክትል ኃላፊው፤ በጋምቤላ የወይና ደጋና ቆላማ የአየር ሁኔታ በስፋት የሚስተዋል በመሆኑ ይህም ለሩዝና ለስንዴ ሰብሎች ምቹ ሁኔታን የሚፈጥር መሆኑን ተናግረዋል።

የመስኖ ልማት ሥራውን ቀደም ብለው የጀመሩ ወረዳዎች መኖራቸውን በማንሳት፤ በክልሉ የሚስተዋለውን የምርጥ ዘር እጥረት ችግር ለመፍታት ከግብርና ምርምር ተቋማት ጋር እየተሠራ መሆኑን አንስተዋል።

እንደ አቶ ዳግም ገለጻ፤ በዘርፉ ላይ የሚስተዋሉ ችግሮችን በመቋቋም የተለያዩ አይነት የሰብል ምርቶችን ለማምረት እንቅስቃሴ እየተደረገ ነው። ከዚህ በተጨማሪም በሌሎች የአትክልትና ፍራፍሬ ምርቶች ላይ በስፋት ለመሥራት ግብ ተቀምጧል።

በአሁኑ ጊዜም ከሰብል አሰባሰብ ጋር ተያይዞ የኮምባይነር እጥረት በመኖሩ የሰው ጉልበት በመጠቀም ሰፊ እንቅስቃሴዎች እየተከናወኑ መሆናቸውን ያነሱት አቶ ዳግም፤ የበቆሎ፣ የሩዝ እና ሌሎች የሰብል ዓይነቶች እየተሰበሰቡ ያሉበት ሁኔታ መኖሩን ጠቁመዋል።



# የቡናን ምርትና ምርታማነት ለማሳደግ አቅሞችን አስተባብሮ መጠቀም ያስፈልጋል

## - ብሔራዊ የቡና ፕላትፎርም ይፋ ተደረገ

**ፋንታነሽ ክንዴ**

አዲስ አበባ፡- የቡናን ምርትና ምርታማነት ለማሳደግ፣ ጥራቱን ለማስጠበቅና የገበያ ዕድሎችን ለማፈላለግ ያለንን አቅም አስተባብሮ መጠቀም እንደሚያስፈልግ የኢትዮጵያ ቡናና ሻይ ባለሥልጣን ዋና ዳይሬክተር አዱኛ ደበላ (ዶ/ር) ገለጹ።

በቡና ላይ የሚሠሩ ባለድርሻ አካላት በትብብር መሥራት የሚያስችል ብሔራዊ የቡና ፕላትፎርም ይፋ ተደርጓል።

የባለሥልጣኑ ዋና ዳይሬክተር አዱኛ ደበላ (ዶ/ር) በመርሐ ግብሩ ላይ ባደረጉት ንግግር እንዳሉት፤ ቡና ላይ የሚሠሩ የተለያዩ ባለድርሻዎች ውጤት ለማምጣት የሚያከናውኑት ሥራ በተበታተነ መልኩ የሚተገበር ነበር። በዚህም ምክንያት ማን ምን እንደሚሠራ የትኛው አካል በየትኛው ፕሮጀክት ላይ እንደሚሠራ ስለማይታወቅ የፕሮጀክቶች መደራረብና ሀብቶችን በአግባቡ ለመጠቀም እንቅፋት ፈጥሮ ቆይቷል።

የፕላትፎርሙ እውን መሆን በተበታተነ መልኩ የሚደረጉ ጥረቶችን የጋራ በማድረግ የቡና ምርትና ምርታማነትን ለማሳደግ፣ ጥራትን ለመጠበቅና የገበያ ዕድሎችን ለማፈላለግ ያስችላል ብለዋል።

ከዚህም በተጨማሪ የአውሮፓ ኅብረት ያወጣውን ከደን ምንጣሮ ነፃ ምርት ሕግን ለማሟላትም ትልቅ አቅም እንደሚሆን ጠቁመዋል።

ኢትዮጵያ የ15 ዓመት የቡና ስትራቴጂ ቀርጻ በመተግበር ላይ መሆኗን አስታውሰው፤ በዚህም ከአምስት አልያም ከስድስት ዓመት በኋላ የቡና ወጪ ንግድ ገቢን 4 ቢሊዮን ዶላር ለማድረስ ታቅዷል። ይህን ለማሳካት ደግሞ ያለንን አቅም አስተባብረን መጠቀም ይኖርብናል ብለዋል።

ፕላትፎርሙ ቡና ላይ የሚሠሩ ባለድርሻ አካላትን የሚያካትት መሆኑን ጠቁመው፤ በቀጣይነትም ቡና ላይ ለመሥራት ፕሮጀክቶችን ይዘው የሚመጡ አካላት ሁሉ የፕላትፎርሙ አባል መሆን እንደሚችሉ ገልጸዋል ።

የገንዘብ ሚኒስትር ዴኤታ ሰመሪታ ሰዋሰው በበኩላቸው፤ ቡና ለኢትዮጵያ አጠቃላይ ሀገራዊ ጥቅል ምርት አምስት በመቶ የሚያበረክትና ከወጪ ንግድ ገቢ 34 በመቶ የሚሸፍን ወሳኝ ምርት መሆኑን አመልክተዋል።

ዘርፉ ለአምስት ሚሊዮን አነስተኛ አርሶ አደሮች የኑሮ መሠረት መሆኑን ጠቅሰው፤ ከዚህ ውስጥ ከ25 እስከ 30 በመቶ የሚሆኑት በአማካይ ግማሽ ሄክታር መሬት ላይ ቡናን የሚያለሙ ሴቶች መሆናቸውን ጠቅሰዋል።

ብሔራዊ የቡና ፕላትፎርም መፈጠሩ ባለድርሻ አካላትን በማስተባበር የቡና ምርት ውጤታማነት ላይ የጋራ ራዕይ ለማስቀመጥ የሚያግዝ ነው ብለዋል።

የአውሮፓ ኅብረት ከአካባቢ ጥበቃ ጋር በተገናኘ ያወጣው ሕግ የኢትዮጵያ ቡና ወጪ ንግድ ላይ ተፅዕኖ የሚያሳድር መሆኑን ጠቅሰው፤ ኢትዮጵያ የአውሮፓ ኅብረትን ተነሳሽነት በምታከናውናቸው የአካባቢ ጥበቃ ላይ ያተኮረ የልማት ፕሮግራሞች ትደግፋለች። ይሁን እንጂ የተቀመጡ ቅድመ ሁኔታዎች ጊዜ የሚፈልጉ ናቸው ብለዋል።

መንግሥት የቡና ዘርፉን ሪፎርም ለማድረግ ከባለድርሻ አካላት ጋር በትብብር እየሠራ መሆኑን አስታውሰው፤ የተቀመጠውን መስፈርት ለማሟላት የሦስት ዓመት እቅድ ተነድፎ የተለያዩ ተግባራትም በመከናወን ላይ ናቸው። የተፈጠረው የትብብር ፕላትፎርም እነዚህን ሥራዎች ለመጋራትና ዘርፉን ይበልጥ ውጤታማ ለማድረግ ትልቅ አቅም እንደሚሆን አመላክተዋል።

# “ሕዝቡ ወንድማማችነቱን በማጎልበት የጽንፈኛና አሸባሪ ኃይሎችን እኩይ ዓላማ ሊያከሽፍ ይገባል”

**- አቶ ኃይሉ አዱኛ**
**የኦሮሚያ ክልል ኮሙኒኬሽን ቢሮ ኃላፊ**

**ማርቆስ በላይ**

አዲስ አበባ፡-ሕዝቡ ወንድማማችነቱን በማጎልበት የጽንፈኛና አሸባሪ ኃይሎችን እኩይ ዓላማ ሊያከሽፍ ይገባል ሲሉ የኦሮሚያ ክልል ኮሙኒኬሽን ቢሮ ኃላፊ አቶ ኃይሉ አዱኛ ገለጹ፡፡

አቶ ኃይሉ አዱኛ በወቅታዊ ጉዳዮች ዙሪያ ለመገናኛ ብዙኃን ትናንት በሰጡት መግለጫ እንዳሉት፣ ሕዝቡ አንድነቱን ጠብቆ ወንድማማችነቱን በማጎልበት የጽንፈኛና አሸባሪ ኃይሎችን እኩይ ዓላማ ሊያከሽፍ ይገባል፡፡

መንግሥት ሁሉንም የፀጥታ አካላት አሰማርቶ የሕግ የበላይነትን በማስከበር የሕዝቡን ሠላምና ደኅንነት ለማስጠበቅ በቁርጠኝነት ይሠራል፡፡

የክልሉ መንግሥት በጽንፈኛ ኃይሎች የተፈጸመውን አሰቃቂ ግድያ አጥብቆ እንደሚያወግዝና ዘላቂ ሠላምን ለማስፈን በትኩረት እየሠራ ይገኛል ያሉት አቶ ኃይሉ፣ መንግሥት የሕግ የበላይነትን በማስከበር የሕዝቡን ሠላምና ደኅንነት ለማስጠበቅ በቁርጠኝነት ይሠራል ብለዋል።

በኦሮሚያ ክልል ሰሜን ሸዋ ዞን ደራ ወረዳ ጽንፈኛው ፋኖ አሰቃቂ ድርጊት መፈጸሙን ጠቅሰው፣ ጽንፈኞች ድርጊታቸው ተመሳሳይና ግባቸውም በኦሮሞና አማራ ሕዝብ መካከል ግጭት መፍጠር፣ ጥላቻን መንዛትና አንድነት እንዳይኖር ማድረግ መሆኑን ገልጸዋል፡፡

ጽንፈኞች ግባቸው አንድ ሲሆን የሚለያዩት በሚናገሩት ቋንቋ ብቻ መሆኑን በመግለጽ፣ ሽብርተኛው ሸኔም አሰቃቂ ግድያዎችን በኦሮሞ ሕዝብ ላይ ሲፈጽም መክረሙን ተናግረዋል፡፡

አሸባሪው ሸኔ የኦሮሞ ሕዝብ ልማቱን እንዳይሠራ በማደናቀፍ፣ ንብረቱን በመዝረፍ፣ አሰቃቂ ግድያዎችን ሲፈጽም መኖሩን ጠቅሰው፣ ሸኔም ሆነ ራሱን ፋኖ ነኝ ብሎ የሚጠራው ጸንፈኛ በሕዝብ ላይ ታሪክ ይቅር የማይለውን ወንጀል መፈጸማቸውን ገልጸዋል፡፡

የክልሉ መንግሥት በአሸባሪው ሸኔም ሆነ ጽንፈኛው ፋኖ የሚፈጽሙትን አሰቃቂ ድርጊት አጥብቆ ይኮንናል ያሉት ኃላፊው፣ መንግሥት በአሸባሪው ቡድን ሸኔና በጽንፈኛው ፋኖ ላይ የሚወስደውን እርምጃ አጠናክሮ ይቀጥላል ብለዋል፡፡

በክልሉ በሚንቀሳቀሰው አሸባሪው ሸኔና በአማራ ክልል በሚንቀሳቀሰውም ጽንፈኛው ፋኖ ላይ ጠንከር ያለ እርምጃ እየተወሰደባቸው እንደሚገኝ ጠቅሰው፣ የጽንፈኛ ኃይሎች እየተወሰደባቸው ያለውን እርምጃ መቋቋም ሲያቅታቸው ሕዝቡን ለማነሳሳት አሰቃቂ ድርጊቶችን በንፁሐን ላይ እየወሰዱ እንደሚገኙ አስረድተዋል፡፡

ጽንፈኞች በድርጊታቸው ሕዝቡ ተጠልፎ ወደ ብሔር ግጭት እንዲገባ፣ ሀገር እንዳትረጋጋና ሠላሟ እንዳይጠበቅ ማድረግ መሆኑን በመግለጽ፣ የክልሉ ሕዝብ የሽብርተኛና ጽንፈኛ ቡድኖችን እኩይ ተግባር በመገንዘብ አንድነቱን፣ ወንድማማችነቱን ሊያጠናክር እንደሚገባው ጠቁመዋል፡፡

የክልሉ ሕዝብ ግጭት እንዲቆም ሠላማዊ ሰልፎችን በመውጣት ጥያቄውን በማቅረቡ መንግሥትም የሕዝቡን ጥያቄ ተቀብሎ እየሠራበት እንደሚገኝ ጠቅሰው፣ የክልሉ መንግሥት ሁሉንም አማራጮች በመጠቀም ሠላምን ለማስፈን እንደሚሠራ ገልጸዋል፡፡

የሽብርተኛው ሸኔ አባላት ሕዝብ ያቀረበውን ጥሪ ተቀብለው ወደ ሠላም እየተመለሱ እንደሚገኝ በመግለጽ፣ መንግሥት የሕዝቡን ጥሪ ተቀብሎ ወደ




ሠላም አማራጮች የተመለሱትን ተቀብሎ ሥልጠና በመስጠት የሚያቋቁማቸው መሆኑን ገልጸዋል፡፡

በመጨረሻም በተለያዩ ቦታዎች ላይ የሚንቀሳቀሱ የሸኔ ታጣቂዎች የተከፈተውን የሠላም በር ተጠቅመው ወደ ሠላማዊ መንገድ እንዲገቡም ጥሪ አቅርበዋል፡፡



# የቀድሞ ታጣቂዎችን በዘላቂነት ለማቋቋም ወደ ተሐድሶ ሥልጠና ማዕከላት የማስገባት ሥራ ተጀመረ

**በጋዜጣው ሪፖርተር**

አዲስ አበባ፡- የቀድሞ የትግራይ ክልል ታጣቂዎችን በዘላቂነት ለማቋቋም ወደ ተሐድሶ ሥልጠና ማዕከላት የማስገባት ሥራ ተጀምሯል። ወደ ተሐድሶ ሥልጠና ማዕከላት የሚገቡ የቀድሞ የትግራይ ክልል ታጣቂዎች ትጥቃቸውን ማስረከብ ይጠበቅባቸዋል።

በዚሁ መሠረትም የመጀመሪያ ዙር የመቀሌ የተሐድሶ ሥልጠና ማዕከል የሚገቡ የትግራይ ክልል የቀድሞ ታጣቂዎች የነፍስ ወከፍ እና የቡድን የጦር መሣሪያ ትጥቃቸውን ለሀገር መከላከያ ሠራዊት አስረክበዋል።

የፕሪቶሪያውን የሠላም ስምምነት ተከትሎ የቀድሞ ታጣቂዎች ከአንድ ዓመት በፊት የከባድና መካከለኛ የጦር መሣሪያ ትጥቃቸውን የአሕጉራዊና ዓለም አቀፋዊ ተቋማት ታዛቢዎች በተገኙበት ለሀገር መከላከያ ሠራዊት ማስረከባቸው ይታወሳል።

በርክክብ ሥነ-ሥርዓቱ ላይም የብሔራዊ ተሐድሶ ምክትል ኮሚሽነርና የመከላከያ ሠራዊት ተወካይ ብርጋዴር ጄኔራል ደርቤ መኩሪያ፣ የመከላከያ ሠራዊት ወታደራዊ መኮንኖች፣ የብሔራዊ ተሐድሶ ኮሚሽነሮች፣ የትግራይ ክልል ጊዜያዊ አስተዳደር ተወካዮች፣ የአፍሪካ ኅብረት፣ የአውሮፓ ኅብረት፣ የተባበሩት መንግሥታት ድርጅትና ሌሎች ተባባሪ አካላት ተገኝተዋል።

የቀድሞ የትግራይ ክልል ታጣቂዎች በየሥልጠና ማዕከላቱ የሚኖራቸውን ቆይታ ካጠናቀቁ በኋላ ከማኅበረሰቡ ጋር ተቀላቅለው መደበኛ ሕይወታቸውን የሚመሩበት የገንዘብና የቁሳቁስ መቋቋሚያ ድጋፍ ይደረግላቸዋል ተብሏል።

የብሔራዊ ተሐድሶ ኮሚሽነር ተመስገን ጥላሁን፤ በትግራይ ክልል መቀሌ፣ እዳጋ ሐሙስ እና ዓድዋ በተዘጋጁ ሦስት ማዕከላት በሚቀጥሉት አራት ወራት 75 ሺህ የቀድሞ ታጣቂዎችን ትጥቅ በማስፈታት በዘላቂነት የማቋቋምና ወደ ማኅበረሰቡ የመቀላቀል ሥራ እንደሚከናወን ማሳወቃቸው ይታወሳል ሲል ኢዜአ ዘግቧል።

# የኢትዮጵያ አየር መንገድ በዓለም አቀፍ አገልግሎት ምርጥ አየር መንገድ በመባል ተሸለመ

**በጋዜጣው ሪፖርተር**

አዲስ አበባ፣ የኢትዮጵያ አየር መንገድ በዓለም አቀፍ አገልግሎት የዓመቱ ምርጥ አየር መንገድ በመሆን ለስምንተኛ ጊዜ ተሸልሟል።

በግብፅ ካይሮ በተካሄደው 56ኛው የአፍሪካ አየር መንገዶች ማኅበር አጠቃላይ ስብሰባ ላይ የኢትዮጵያ አየር መንገድ በዓለም አቀፍ አገልግሎት የዓመቱ ምርጥ አየር መንገድ በመባል ሽልማቱን ማሸነፉ ተገልጿል። አየር መንገዱ ሽልማቱን ሲያሸንፍ የአሁኑ ለ8ኛ ጊዜ መሆኑ ተነግሯል።

የአየር መንገዱ የተሰጠው እውቅና ለአገልግሎቱ፣ ለትርፋማነቱ፣ ከሌሎች ተቋማት ጋር ያለው ትብብር፣ በአሕጉሪቱ በካርጎ አገልግሎት እድገት እና አፍሪካን ከተቀረው ዓለም ጋር የሚያገናኝ ላቅ ያለ የሥራ አፈጻጸም በማስመዝገቡ ነው ተብሏል።

የኢትዮጵያ አየር መንገድ ግሩፕ ዋና ሥራ አስፈፃሚ አቶ መስፍን ጣሰው ባደረጉት ንግግር እንዳሉት፥ ሽልማቱ የአየር መንገዱ ቁርጠኝነት እና ጽናት ማረጋገጫ ነው።

በተጨማሪም ሽልማቱ የአፍሪካን ትስስር ለማሳደግና የኢኮኖሚ እድገትን ለማቀጣጠል ያለንን የማይናወጥ ተልዕኮ የሚያሳይ ነው ሲሉ አንስተው፤ ለዚህም ለተጉ ሁሉ ምስጋና አቅርበዋል።

በአሠራር ብቃቱ እና ስኬታማነቱ በአፍሪካ ተወዳዳሪ የሌለው የኢትዮጵያ አየር መንገድ ለደንበኞች ምቹ የሆነ ዓለም አቀፍ ተደራሽነትና የጉዞ ልምድን ማበርከቱን ቀጥሏል ብለዋል ዋና ሥራ አስፈጻሚው።

የኢትዮጵያ አየር መንገድ ኔትወርክን በማስፋት፣ በዘመናዊ አውሮፕላኖች ላይ ኢንቨስት በማድረግ እና ዓለም አቀፍ ደረጃውን የጠበቀ የደንበኞች አገልግሎት በመስጠት አሕጉሩን ለማገልገል ያለውን ቁርጠኝነት ማሳየቱን ጠቁመዋል።

# ርዕሰ አንቀፅ

## ታጣቂዎችን ትጥቅ አስፈትቶ ወደ ተሐድሶ ማዕከላት ማስገባት ከግጭት ለመውጣት የሚያስችል መልካም መንገድ ነው !

የሠላም ጉዳይ የቱን ያህል ዋጋ እንዳስከፈለን የቀደሙ ሥልጣኔዎቻችንን እና አሁን ላይ ያለንበትን ሀገራዊ እውነታ ማጤን በራሱ በቂ እና ከበቂ በላይ ነው። ችግሩ ከአንድ ትልቅ ሀገራዊ ከፍታ አውርዶን አሁን ላይ ላለንበት ድህነት እና ኋላ ቀርነት ዳርጎናል። በቀጣይ ዕጣ ፈንታችን ላይ ሊያሳድር የሚችለውም ተፅዕኖ ቀላል አይሆንም ።

በዘመናት ውስጥ ልዩነቶችን/ችግሮችን በሰከነ መንፈስ ሀገር እና ሕዝብን ተጠቃሚ በሚያደርግ ውይይት እና ድርድር  መፍታት የሚያስችል ባሕል መፍጠር አለመቻላችን፤ ከዚህ ይልቅ በግትርነት እና በኃይል ለነገሮች መፍትሔ ለመስጠት የሄድንባቸው መንገዶች በግጭት አዙሪት ውስጥ እንድንዳክር አድርገውን ቆይተዋል ።

ይህም ሕዝባችን ለዘመናት የሚናፍቀውን ልማት እውን አድርጎ፤ ለቀደሙት የገናናነት ትርክቶቹ ትንሳኤ ለመስጠት  በየዘመኑ ያደረጋቸውን ጥረቶች አምክኖታል፤ መነቃቃቱንም አደብዝዞታል። በዚህም ትውልዶች ሕልማቸውን መኖር የሚችሉበት ሀገራዊ የፖለቲካ ምሕዳር አጥተው ሕልማቸውን ከሸፎ ለማለፍ ተገድደዋል ።

አሁን ያለውም ትውልድ ቢሆን በአዲስ የተሐድሶ መንፈስ፤ ከፍ ባለ መነቃቃት የሀገሩን ዕጣ ፈንታ ለመቀየር በቁጭት የጀመረው የለውጥ ጎዳና በተመሳሳይ ተግዳሮቶች ውስጥ ለማለፍ የተገደደበት ሁኔታ ተፈጥሯል። በተለመደው የፖለቲካ ባሕላችን ተፈትኖ በብዙ መንገራገጮች ውስጥ አልፏል ።

በአንድ በኩል የፖለቲካ ልዩነቶችን በኃይል የመፍታት አስተሳሰብ ስብራት ውስጥ ያለ፤ በዚህም አተርፋለሁ ብሎ የሚያምን ኃይል፤ በሌላ በኩል ይህ አይነቱ እሳቤ ለሀገርም ለሕዝብም ከዚያም ባለፈ ሀሳቡን ለሚያራምደውም ቡድን አትራፊ ሊሆን አይችልም በሚል ኃይል መካከል የተፈጠረው የአስተሳሰብ ተቃርኖ ሀገርን ዳግም ወደ ግጭት ወስዷታል።

ግጭቶቹ ሺዎችን ለሞት እና አካል ጉዳት ዳርጓል፤ ሚሊዮኖችን ከሞቀ ቤት ንብረታቸው አፈናቅሏል፤ በትሪሊዮን የሚገመት የሀገር ሀብት አውድሟል። ከግጭቶቹ ጋር በተያያዘ በዜጎችን ላይ ከፍ ያለ፤ እስካሁን ያላገገመ የሥነ ልቦና ስብራት ተፈጥሯል። ግጭቶቹ የፈጠሩት ሀገራዊ የኢኮኖሚ መንገጫገጭም መላውን ሕዝባችንን ዛሬ ድረስ ዋጋ እያስከፈለ ነው።

ቀደም ብሎ እንደተገመተውም በእነዚህ ግጭቶች ሀገር እና ሕዝብ ላልተገባ ችግር ተዳረጉ እንጂ ማንም ተጠቃሚ አልሆነም ። ለሕዝባችን አዲስ የለውጥ ጉዞ ፈተና ሆነ እንጂ የትኛውንም ቡድን አሸናፊ አላደረገም። ይዘነው የመጣነው ፖለቲካ ባሕል የቱን ያህል አጥፊ እንደሆነ ለትውልዱ ተጨባጭ ማሳያ ሆነ እንጂ ማንንም አላተረፈም።

ልዩነቶችን በኃይል ለመፍታት የሚደረጉ የትኛውም አይነት ጥረቶች፤ ከትናንት እስከ ዛሬ ካስከፈሉን እና እያስከፈሉን ካለው ያልተገባ ዋጋ አንጻር እውነታውን በኃላፊነት መንፈስ ቆም ብለን ልናስብ ይገባል። ይህ የአስተሳሰብ ስብራት በዘመናት መካከል ለሕዝባችን ተስፋ ጥላ ሆነ የቆመ እርግማን መሆኑን በአግባቡ ልናስተውል ይገባል።

በተለይም ሀገር ተረካቢው፤ የነገይቱ ኢትዮጵያ ተስፋ የምታደርገው ወጣቱ ትውልድ፤ ይህ የአስተሳሰብ ስብራት በቀደሙት ዘመናት የነበሩ ወጣቶችን ተስፋ የነጠቀ፤ ሕልማቸውን ኖረው እንዳያልፉ ዋነኛ ተግዳሮት እንደነበረ ሊረዳ እና የዚህ ስብራት ሰለባ እንዳይሆን በጥንቃቄ መጓዝ ይገባዋል ።

የትኛውም አይነት የኃይል አማራጭ በብዙ የተስፋ ዲስኩሮች ቢታጀብ፤ የትውልዱን ዛሬ እና ነገዎች ከመብላት ባለፈ፤ የተስፋው ባለቤት ሊያደርገው አይችልም፤ ለዚህ ደግሞ ባለፉት ዘመናት የመጣንባቸው የግጭት/የኃይል  መንገዶች   ተጨባጭ ማሳያዎች ናቸው። የነበረውን ከማሳጣት፤ ተስፋ ያደረገውን ከመናጠቅ ያለፈ ፋይዳ አልነበራቸውም።

በነዚህ ግጭቶች ውስጥ በሀገር አቀፍ ደረጃ ተሳታፊ የነበሩ ታጣቂዎችን በዘላቂነት ለማቋቋም ትጥቅ የማስፈታትና ወደ ተሐድሶ ማዕከላት የማስገባት ሥራም ይህንን በዘመናት ብዙ ዋጋ ሲያስከፍለን የነበረውን የአስተሳሰብ ስብራት የማከም፤ ለሀገራዊ ተስፋችን ጥላ ከሆነው የግጭት አዙሪት ለመውጣት የሚያስችለን የመታረም መንገድ ነው!


# አዲስ ዘመን

ግንቦት 30 ቀን 1933 ዓ.ም ተቋቋመ

**የኢትዮጵያ ፕሬስ ድርጅት ዋና ስራ አስፈጻሚ**
ስልክ ቁጥር - 011-126-42-22
ኢሜል :- epa@press.et

**ዋና አዘጋጅ**
አንተነህ ኃ/ብርሃን ወ/መድህን

**አድራሻ**
ንፋስ ስልክ ላፍቶ ክ/ከ
ወረዳ 06
የቤት ቁጥር 319
ኢሜይል - anteneh.hailebirhan@press.et
ስልክ ቁጥር - 011-1-26-42-40

**የገበያ ልማትና ፕሮሞሽን ዘርፍ**
ኢሜይል - etpresspromotion@gmail.com
ስልክ - 011-126-43-41
ፋክስ - 011-811-13-15
የዝግጅት ክፍል ፋክስ - 251-011-1-56-98-62

**የአዲስ ዘመን ማኔጂንግ ኤዲተር**
ወንድወሰን ሽመልስ ታደሰ
ስልክ፡- 011 126 4200
Email:- wendweson.shimelis@press.et
wendwesonshimelis@gmail.com

**የዜና ማዕከል ዋና አዘጋጅ**
ወርቁ ማሩ
Email:- workumaru2@gmail.com

**የአዲስ ዘመን ምክትል ዋና አዘጋጆች**
- ኃይሉ ሣህለድንግል
- እስማኤል አረቦ
- ቦጋለ አበበ

**የማስታወቂያ መቀበያ ክፍል**
ስልክ ቁጥር - 011-156-98-73
ፋክስ - 011-126-58-12
ቴሌግራም - 097- 608-47-07 - Press

**የማስታወቂያ ሽያጭ ማስተባበሪያ**
ስልክ - 011-1-26-43-39

**ማከፋፈያ** :- ስልክ ቁጥር - 011-157-02-70


# ነፃ ሃሳብ

ይህ አምድ በተለያዩ ፖለቲካዊ ኢኮኖሚያዊና ማህበራዊ ጉዳዮች ዙሪያ ዜጎች ነፃ ሀሳባቸውን የሚሰጡበት ነው።፡በዓምዱ ላይ የሚወጡ ጽሁፎች የዝግጅት ክፍሉን አቋም አያመለክቱም።፡

## ‘ሃይ ባይ!’ ያጣው የታክሲዎች ማቆራረጥና ከታሪፍ በላይ ማስከፈል

ሜሉዲ ከኳስ ሜዳ

ኢትዮጵያ በተለይ ካለፈው ዓመት ወዲህ በአዲስ አበባ ከተማ እያከናወነች ባለችው የኮሪደር ልማት ከተማዋን ለነዋሪዎቿ ምቹ የመኖሪያና የመሥሪያ ከተማ፣ ጎብኚዎችንና እንግዶችን የምትስብ ከማድረግ አኳያ ስኬቶችን እያስመዘገበች ትገኛለች። የአፍሪካም ሆነ የኢትዮጵያ መዲና በሆነችው አዲስ አበባ ከተማ እየተከናወነ ያለው ልማት ከተማይቱ እንደስሟ ውብ እና ማራኪ ከማድረግ በዘለለ ሃገሪቱን በአጭር ጊዜ ውስጥ በዓለም ላይ ለቱሪዝም ተመራጭ ከሆኑ ከተሞች አንዷ እንደሚያደርጋት አያጠራጥርም።

የከተማዋን መልማት ነዋሪዎቿም ለዘመናት ሲመኙትና ሲናፍቁት የነበረ ጉዳይ በመሆኑ በፍፁም ቅንነት ለልማቱ ስኬት አጋርነታቸውን እያረጋገጡ ይገኛሉ። በከተማይቱ እየታየ ያለው ፈጣንና ማራኪ የልማት ሥራ ተጠናቆ ለማየት ከመጓጓት ባለፈ ከኖሩበት ቀዬ በመነሳታቸውም ሆነ በልማት ሥራው በመንገድ ላይ በሚፈጠሩ መጨናነቆች ምንም አይነት ቅሬታ አላሰሙም። ይልቁንም ከመቼውም ጊዜ በላይ ከመንግሥት ጎን በመቆም  ልማቱ በሁሉም የከተማዋ መንደሮች ዘልቆ እንዲገባ እየጎተጎቱ ይገኛሉ።

አብዛኞቻችን የከተማዋ ነዋሪዎች እንደምናውቀው የኮሪደር ልማቱን ተከትሎ ለጥቂት ጊዜያት ቢሆን በተለይ ዋና ዋና የሚባሉ የከተማዋ መንገዶች በመዘጋታቸው አሽከርካሪዎች ተለዋጭ መንገዶችን ለመጠቀም ተገደው እንደነበር ይታወሳል። በዚህ ምክንያትም በተለይም የታክሲ አሽከርካሪዎች በነባሩ ታሪፍ ላይ በእጥፍ ዋጋ በመጨመር አገልግሎት ሲሰጡ ቆይተዋል። እንዲያም ሆኖ ግን ነዋሪው ልማቱ ቶሎ እንዲጠናቀቅ ካለው ፍላጎት በመነጨ የታክሲ አሽከርካሪዎች በሚያደርጉት አላግባብ የታሪፍ ጭማሪም ያልተገባ መንገድ ማቆራረጥ እምብዛም አላጉረመረመም።

በአሁኑ ወቅት አብዛኞቹ ዋና ዋና መንገዶች ግንባታቸው ተጠናቆ ወደ ቀድሞ አገልግሎታቸው ቢመለሱም በተለይ ታፔላ ተሰጥቷቸው የሚሠሩ ታክሲዎች አሽከርካሪዎች ወደ መስመሩ ሙሉ ለሙሉ ገብተው በአግባቡ መሥራት ሲገባቸው ሕዝቡን እያንገላቱ ይገኛሉ። ከተመደበው ታሪፍ በላይ ከማስከፈላቸውም ባሻገር ዋናውን መስመር በመተው እና አቋራጭ መንገዶችን በመጠቀም ተሳፋሪውን በማይፈልገው መስመር በማጓጓዝና ካሰበበት ሳይደርስ እንዲወርድ በማድረግ ሲያማርሩት ይስተዋላሉ።

ለአብነት መጥቀስ ካስፈለገ ከመገናኛ-ቀበና-አራት ኪሎ ፒያሳ የሚዘልቀውን መስመር ማንሳት ይቻላል። ለእዚህ መስመር ከኮሪደር ልማቱ በፊት ከመነሻ እስከ መዳረሻ ወይም ከመገናኛ እስከ ፒያሳ በይፋ የሚታወቀው ታሪፍ 13 ብር ከሃምሳ ሳንቲም ሆኖ ግን 15 ብር ይከፈል እንደነበር አስታውሳለሁ።

የኮሪደር ልማቱን ተከትሎ የተወሰነው መንገድ በመዘጋቱና አሽከርካሪዎች የአዋሬን አስፋልት ለመጠቀም ተገደው በነበረበት ወቅት ስምንት ብር ከሃምሳ ሳንቲም ተመድቦለት የነበረውን ታሪፍ ተሳፋሪው 10 ብር ይከፈልበት የነበረውና ከመገናኛ አራት ኪሎ መንገድ ፒያሳ ለሚዘልቀው እኩል 20 ብር እንዲከፍል ይጠየቅ ነበር። ይህም ቢሆን ተሳፋሪው ያለውን ነባራዊ ሁኔታ በመረዳት የተጠየቀውን ሲከፍል ቆይቷል፤ ምቹ ያልሆነና ራቅ ያለ ቦታ እንዲወርድ ሲጠየቅም የተባለውን ሲፈጽምም ነበር።

መንገዱ ተጠናቆ ወደ ቀድሞ አገልግሎቱ ከተመለሰ በኋላም ግን አብዛኞቹ የታክሲ አሽከርካሪዎች ወደ ቀድሞው ታሪፍ ለመመለስ ፍቃደኝነታቸውን አላሳዩም። አቋራጩ መንገድ ሕዝብን ለማጭበርበር ይበልጥ አዋጭ ስለሆነላቸው  በነበረው መስመር (ከመገናኛ ቀበና አራት ኪሎ ፒያሳ) ለመሄድ አይሹም።

በዚህ ምክንያት በርካታ የመዲናዋ ነዋሪዎች ለሰዓታት ታክሲ ጥበቃ ይንከራተታሉ፤ በትክክለኛው መስመር ለመሄድ አንድ ፈቃደኛ የሆነ ታክሲ ሲመጣ ለመግባት በሚደረግ ግፊያ በተለይ አቅመ-ደካሞች፣ ነፍሰጡሮች እና ሕፃናት ወድቀው የሚጎዱበት ሁኔታንም ታዝቤያለሁ። ይህንን ተገን አድርጎ የሰው ኪስ የሚገባውም የመገናኛን ሌባ መኖሩን መቼም መናገር አይጠበቅብኝም!።

ይህንን ሁሉ ስቃይ አልፎ መግባት የቻለው ተሳፋሪም ቢሆን በተለይ አራት ኪሎን ተሻግሮ መውረድ የሚሻ ከሆነ ስቃዩ ገና አላበቃለትም። እንዴት? ካላችሁኝ ላስረዳችሁ፤ ነገሩ እንዲህ ነው፤ የዛሬ አጀንዳዬ ዋነኛ ርዕሰ-ጉዳይ የሆኑት እና ሃይ ባይ ያጡት የታክሲ አሽከርካሪዎች ከመገናኛ ተነስተው ልክ እንግሊዝ ኤምባሲ ጋ ሲደርሱ በአዋሬ መታጠፊያ ይታጠፉሉ፤ በገዛ ፍቃዳቸው መንገድ ቀይረው ተሳፋሪውን የረጅም ርቀት እንዲከፍል ያደርጉታል፡፡

እንግዲህ እዚህ ጋር ልብ ማለት የሚገባው ጉዳይ እነዚህ አሽከርካሪዎች ከተሰጣቸው ታፔላ ውጭ የሚሄዱ መሆኑ ነው። ከታሪፍ በላይ እንዲከፍሉ ከመደረጉም በላይ ከሁሉ የሚብሰው ደግሞ ተጠቃሚውን ማዕከል ባላደረገ መልኩ እነሱ በሚሹት ቦታ ብቻ ማውረዳቸው ነው።

ለዚህም ቀድሞ ባነሳሁት መስመር በተለይም አራት ኪሎ ተሻግሮ (ብርሃንና ሰላም ማተሚያ ድርጅት ጋር) መዳረሻው የሆነ ተሳፋሪ ከታሪፍ በላይ እንዲከፍል ተደርጎም እነሱ እንዲመቻቸው ሲሉ አደባባዩን በመዞር እና አብሮኖት ቤተ-መጽሐፍት ጋ እንዲወርድ ያስገድዱታል።

በጣም የሚያሳዝነው ደግሞ አሽከርካሪው እና ረዳቱ ተሳፋሪውን ከሚጠበቀው በላይ ከፍሎም ረጅም ርቀት በእግሩ እንዲሄድ አድርገው ቅሬታ ቢያሰማ ስድብና ዘለፋ ገፋ ካለም ወደ መማታት የሚከጅላቸው ወቅት ያለ ስለመሆኑ በተደጋጋሚ ተመልክቻለሁ። እኔም አንዷ የገፈቱ ቀማሽ ነበርኩ።

ከዚህ ጋር ተያይዞ በቅርቡ ያጋጠመኝን ልንግራችሁ እወዳለሁ፤ አንድ የሥራ ቀን እኔም ሆንኩ አስር ተሳፋሪዎች ከመገናኛ ወደ አራት ኪሎ ፒያሳ እንዲሄድ ታፔላ በተሰጠው ተሽከርካሪ በአንድ የመንገድ ትራንስፖርት ተቆጣጣሪ አስገዳጅነት ተሳፍረን ገባን። አራት ኪሎ (ሥላሴ ቤተክርስቲያን) ጋ ስንደርስ የአራት ኪሎ ተሳፋሪዎች ሁላችንም እንድንወርድ በረዳቱ ተጠየቅን፤ አንዳንዶቹ ተሳፋሪዎች ፈርተው ሲወርዱ እኔና አንድ ሌላ ተሳፋሪ መውረጃችን አልደረሰምና እንሻገራለን ብለን ቁጭ አልን።

‹‹ውረዱ!፤ አንወርድም!›› ጭቅጭቅ ተነሳ፤ በተለይ ረዳቱና ሌላኛው ተሳፋሪ አምባጓራቸው በረታ፤ ተሳፋሪው ዋጋ እንደሚጨምርለት ቢነግረውም ረዳቱ ግን ፀያፍ ስድብ ማውረዱን ቀጠለ፤ ተው ቢባልም ለያዥ ለገራዥ አስቸገረ፤ እናም ልክ ብርሃንና ሰላም ማተሚያ ቤት ስንደርስ የመኪናው በር እንደተከፈተ ተሳፋሪውና ረዳቱ ለድብድብ ተያያዙ፤ ሹፌሩም ከመገላገል ይልቅ ለረዳቱ ተደርቦ ለሁለት ተሳፋሪውን በቦክስና በእርግጫ አጣደፉት።

እኔም ሆንኩ ሌሎች ተሳፋሪዎች ለመገላገል ብንሞክርም የሚቻል አልሆነም፤ ሌሎች ተሳፋሪዎች፣ በተለይ ሽምገል ያሉ አንድ ሰው ሊገላግሉ እሳቸውም የዱላው ተቋዳሽ በመሆናቸው ጩኸትና ግርግሩ በረታ፤ ይሄን ጊዜ ብርሃንና ሠላም ማተሚያ በር ላይ የነበሩ ወታደሮች ሮጠው መጡ፤ እነሱ ባይመጡና አደብ ባያስጓዟቸው ኖሮ ይደርስ የነበረው አደጋ ከዚህም የከፋ ይሆን ነበር!፡፡

እንግዲህ ይህንን ገጠመኝን አብነት አድርጌ አቀረብኩ እንጂ የዚህ መንገድ የዘወትር ተጠቃሚ የሆነ ሰው ከዚህም የባሰ ችግር እንደሚያጋጥመው አልጠራጠርም!። የአሽከርካሪዎችን ስምሪት የሚቆጣጠረው የመንግሥት አካልም ይህንን ችግር አላስተዋለም ብዬ አላምንም።

ምክንያቱም ደግሞ በተለይ መነሻ ላይ አሽከርካሪዎች የሕዝብ አገልጋይነታቸውን በመዘንጋት ለጥቅማቸው ብቻ ቆመው እነሱ ባሻቸው መስመር ብቻ ካልሄድን ብለው ከተቆጣጣሪው አካል ባልደረቦች ጋር የሚያደርጉት እሰጣ አገባ የየቀኑ ገጠመኝ በመሆኑ ነው።

ይህ ተቆጣጣሪ አካል አሽከርካሪዎችን በልልምጥና በማግባባት ብቻ እንዲጭኑ ከማድረግ ባሻገር የማስገደድ ኃላፊነቱን ሊወጣ ይገባል የሚል እምነት አለኝ። በተለይ ለልማትና ለመሳሰሉት ሥራዎች ሲባል የተፈጠረውን ምቹ ሁኔታ አለአግባብ በመጠቀም ሕዝብን እያንገላቱና ላልተገባ ወጪ እያደረጉ ያሉ አሽከርካሪዎችን አደብ ሊያስገዛ ይገባል።

ይህን ሁሉ ስል ግን በታማኝነት በሕዝብና በመንግሥት የተሰጣቸውን ኃላፊነት የሚወጡ ቅን አሽከርካሪዎች የሉም ማለት እንዳልሆነ እንድትረዱልኝ እሻለሁ!። በታፔላቸው የማይሠሩትም ሆነ እያቆራረጡ በመጫን አላግባብ ትርፍ የሚያግበሰብሱት፣ ሕዝብን ለእንግልትና ላልተገባ ወጪ የሚዳርጉት እነዚህ ሕገወጦች ‘ሃይ ባይ!’ ይሻሉ የሚል መልዕክቴን አስተላልፌያለሁ!።

# በኢትዮጵያ ለጨርቃጨርቅ...

**ከ1ኛ ገጽ የዞረ**

ሄክታር መሬት ውስጥ ማልማት የቻለችው 30 በመቶ ብቻ ነው።

ኢትዮጵያ ያላት ሰፊ የተፈጥሮ ሀብት በዓለም አቀፍ የጨርቃጨርቅ ኢንቨስትመንት ተመራጭ እያደረጋት መሆኑን ገልጸው፤ በቀጣይ ያላትን የተፈጥሮ ሀብት በሚፈለገው ደረጃ በማልማት ጥቅም ላይ ማዋል እና ተመራጭነቷን ማሳደግ እንደሚገባ ገልጸዋል።

የኢትዮጵያ የጨርቃጨርቅ እና አልባሳት ወጪ ንግድ ካለፉት ጊዜያት መሻሻል ማሳየቱን አመልክተው፤ እ.ኤ.አ. በ2030 የኢትዮጵያ የጨርቃጨርቅ እና አልባሳት ወጪ ንግድ ከአንድ ቢሊዮን ዶላር በላይ ለማድረስ መታቀዱን ተናግረዋል።

ኢትዮጵያ ባለፉት አስርት ዓመታት ከፍተኛ የኢኮኖሚ እድገት እያስመዘገበች ሲሆን፤ መንግሥትም የግሉን ሴክተር ለማበረታታት ምቹ የንግድ ከባቢን የመፍጠር እና የኢኮኖሚ ማሻሻያ ማድረጉን አስታውቀዋል።

አዳዲስ የኢንቨስትመንት ዕድሎችን የመክፈት፣ የተከለከሉ የኢንቨስትመንት ዘርፎችን የመፍቀድ እንዲሁም የልዩ ኢኮኖሚ ዞኖች አዋጅ የማፅደቅ፣ በሎጂስቲክስ፣ በማኑፋክቸሪንግ፣ በአገልግሎት፣ በነፃ ንግድ እና በሌሎች ዘርፎች ላይ የግል ሴክተሩን የሚያበረታቱ ማሻሻያዎች መደረጋቸውን አብራርተዋል።

በሌላ በኩል በአዲስ አበባ የተካሄደው ዓለም አቀፍ የበፍታህ ጨርቃጨርቅ ፎረም የኢትዮጵያን ቀጣይነት ያለው የኢንዱስትሪ እድገት ራዕይ ለመግለፅ እና በጨርቃ ጨርቅ ዘርፎች ውስጥ ያሉትን ልዩ ዕድሎች ለማስተዋወቅ ወሳኝ መድረክ መሆኑን አስታውቀዋል።

ኢትዮጵያ ያላት የአየር ንብረት እና የአፈር ሁኔታ ለተልባ ምርት ተስማሚ በመሆናቸው በማደግ ላይ ባለው ጨርቃጨርቅ ገበያ ውስጥ ተሳታፊ እንድንሆን ዕድል ይፈጥራል ሲሉ ተናግረዋል።

በኪንግደም ኢትዮጵያ ድርጅት የሎጂስቲክስ ማናጀር ቤተልሔም ቃሲም በበኩላቸው እንደገለጹት፤ ኪንግደም ኢትዮጵያ የተልባ ግንድን ወደ ክር ቀይሮ የሚያመርት በአፍሪካ የመጀመሪያው ድርጅት ነው።

ድርጅቱ የተልባ ግንድን ከፈረንሳይ አስመጥቶ ለሽመና አገልግሎት የሚውል ሊነን የሚባል ክርን አምርቶ ወደ 27 የተለያዩ የዓለም ሀገራት የሚልክ መሆኑን አስታውቀዋል።

የሊነን ክር ለዓለም ሀገራት ለማስተዋወቅ እና ኢትዮጵያ ለኢንቨስትመንት ምቹ ሀገር መሆኗን ለማስተዋወቅ የሚረዳ ዓለም አቀፍ የበፍታህ ጨርቃጨርቅ ፎረም አዘጋጅተን በአዲስ አበባ አካሂደናል ብለዋል።

ፋብሪካው ሥራ ከጀመረ አራት ዓመታትን ያስቆጠረ ሲሆን ለአንድ ሺህ 200 ሠራተኞች ቋሚ የሥራ ዕድል መፍጠሩን ገልጸዋል።

ኢትዮጵያ የፋብሪካውን ጥሬ እቃ ለማምረት ምቹ የተፈጥሮ ሀብት ያላት በመሆኑ በሀገር ውስጥ ለመተካት ጥረት እየተደረገ መሆኑን አመላክተዋል።

# "የስታርት አፕ"...

**ከ1ኛ ገጽ የዞረ**

የማኅበረሰቡን ችግር የሚፈታ፣ ቴክኖሎጂን መርሕ ያደረገ እንዲሁም ዓለም አቀፍም መሆን የሚችል ዘርፍ ነው ይላሉ። የስታርት አፑ ዘርፍ የሀገሪቱ የወደፊት ዋነኛው የኢኮኖሚ ዋልታነቱን ለማስመስከርም የአምስት ሚሊዮን ኮደርስ ሥልጠና፣ የአዕምሯዊ ንብረት ምዝገባ መጠናከርና የኢኖቬሽንና ቴክኖሎጂ የፖሊሲ ማሻሻያዎች ትግበራ አስፈላጊ መሆኑን ያስረዳሉ ።

በተለይ የካፒታል ገበያ የስታርት አፕ ምሰሶ ነው የሚሉት ተመራማሪው፤ ካፒታል ገበያ ገንዘብ ያላቸው አካላትና ሃሳብ ያላቸው አካላት የሚገናኙበት ነው። ስታርት አፕ በሀገር ኢኮኖሚና ቴክኖሎጂ ዘርፎች ከሚያስገኘው ተጠቃሚነት ጎን ለጎን የውጭ ምንዛሪም ለማስገኘት፣ ሌሎች ተቋማት አምራች እንዲሆኑ እንዲሁም ወጣቶች በቀጥታ ዓለም አቀፍ ኩባንያዎች ውስጥ እንዲቀጠሩ የሚያስችል መሆኑን ነው የገለጹት።

ኢንቨስትመንት ባንክ ተቋቁሞ ስታርት አፖች በካፒታል ገበያው ላይ እንዲካተቱ ከተደረገ፣ በቅንጅት መሥራት እንዲሁም የአሠራር ሥርዓቱ ማዘመን ከተቻለ የተሻለ ውጤት ማግኘት የሚቻልበት ቢሆንም በዓለም ባለው ልምድ 90 በመቶ ውጤታማ ላይሆን የሚችልበት ሁኔታ በመኖሩም ጥንቃቄ ማድረግ ያስፈልጋልም ባይ ናቸው።

እንደ ተመራማሪው ገለጻ፤ ከዚህ በፊት ባለው ልምድ የቢዝነስ ሃሳብ ያላቸውና ጀማሪ ሰዎች ያለ ማስያዥያ ብድር ሊያገኙ አይችሉም። ሀብት ያላቸው ሰዎች ብቻ ተጨማሪ ሀብት እንዲሠሩ የሚያበረታታ ነበር፤ ለአብነትም ባለፉት ዓመታት በኢትዮጵያ ከተሰጠ ብድር 23 በመቶ የሚሆነው አስር ተቋማትና ግለሰቦች ብቻ መውሰዳቸውን የብሔራዊ ባንክ ሪፖርት ያሳያል።

ኢትዮጵያ አዳዲስ ቢዝነስ ለመጀመር ከሚያበረታቱ ሀገራት በዓለም 159ኛ ደረጃ ላይ እንደሆነች መረጃዎች ይጠቁማሉ የሚሉት ተመራማሪው፤ ፈቃድ ለመውሰድ ያለው እንግልት፣ ቢሮክራሲ፣ ሙስናና ሌሎች አስቸጋሪ ሁኔታዎች ከሚፈጥሩ ጉዳዮች መካከል ተጠቃሽ መሆናቸውን ያመላክታሉ።

ለስታርት አፕ አዲስ ጅማሮ በመሆኑ የበለጠ ከባድ እንዳይሆን የተለያዩ ማሻሻያዎችና የአሠራር ሥርዓቶች ቀድሞ መዘርጋት እንደሚያስፈልግ ይጠቁማሉ።

የስታርት አፕ ዘርፉን ለማሳደግም የስታርት አፕ ጉዳዮችን ብቻ የሚያይ ተቋም መመሥረት ካለም አጠናክሮ ማስቀጠል፣ ግንዛቤ መፍጠር፣ ሃሳቦችን የሚያስተናግድ በየክልሉ ቢሮ መክፈት፣ ሥልጠና መስጠት እንዲሁም በጀት የሚመቻችበት ሁኔታ መፍጠር ያስፈልጋል ባይ ናቸው።

የኢኖቬሽንና ቴክኖሎጂ ሚኒስትር በለጠ ሞላ (ዶ/ር) በ16ኛው የዓለም አቀፍ የኢንተርፕርነርሺፕ ሳምንት መክፈቻ ላይ እንደገለጹት፤ ሚኒስቴር መሥሪያ ቤቱ ለስታርት አፖች የሚሆን ግልጽ የፖሊሲ እና የፋይናንስ ድጋፋ ማሕቀፍ ተዘጋጅቶ እየተሠራ ነው።

የተለወጠች ኢትዮጵያን እውን ማድረግ እንዲቻል በፈጠራ ላይ የተመሠረተ ኢኮኖሚ ማሳደግ የግድ ይላል የሚሉት በለጠ (ዶ/ር)፤ የስታርት አፕ ዘርፍ ማኅልበት ለዚህ ወሳኝ መሆኑን ይጠቁማሉ።

የተሻለ ሀገር ለመገንባትም በፖለቲካል ኢኮኖሚ ውጤታማ ተሞክሮ ካላቸው ሀገራት ልምድ መውሰድ ተገቢ ስለመሆኑ ያክላሉ።

እንደ በለጠ (ዶ/ር) ገለጻ፤ በስታርት አፑ ዘርፍ ለሥራ ፈጣሪው በፖሊሲ ምቹ ሁኔታዎች መፍጠር የቻሉ ሀገራት የተሻለ ኢኮኖሚ ማስመዝገብ ችለዋል። ሥራ ፈጣሪው ሃሳቡን አደራጅቶ ወደ ሥራ መግባት የሚችልበትን ዓውድ ማመቻቸት እንዲሁም አስፈላጊውን ሀብትና የፖሊሲ ማዕቀፍ ማዘጋጀት ያስፈልጋል።

በለጠ (ዶ/ር)፤ የትኛውም ዘርፍ በቴክኖሎጂ መደገፍ ካልተቻለ ውጤታማ ሥራ መሥራት እንደማይቻል ጠቅሰው፤ የስታርት አፕ ዘርፉ ሀገሪቱ ወደ ኢኮኖሚና ቴክኖሎጂ ሽግግር ማስገባት የሚችል ነው ይላሉ።

የአዕምሯዊ ንብረት ምዝገባ መጠናከር ለሀገሪቱ ኢኮኖሚና ፈጠራ ዘርፍ መጎልበት ከፍተኛ ሚና አለው የሚሉት ደግሞ የኢትዮጵያ አዕምሯዊ ንብረት ባለሥልጣን ዋና ዳይሬክተር አቶ ወልዱ ይመስል ናቸው።

የአዕምሯዊ ንብረት ምዝገባ መጠናከር የውጭ ኢንቨስትመንት ከማሳደግ ጎን ለጎን በየዘርፉ ፈጠራ ላይ ለተሰማሩ ዜጎች ተጠቃሚ የሚያደርግና ለፈጠራ እንዲነሳሱ እንዲሁም የቴክኖሎጂ ሽግግር እንዲኖር የሚያግዝ መሆኑንም ነው የሚያስረዱት።

በተለይ ስታርት አፕ ከፍተኛ የአዕምሯዊ ንብረት ምዝገባ የሚሻ ነው የሚሉት አቶ ወልዱ፤ የአዕምሯዊ ንብረት ምዝገባው በተጠናከረ ቁጥር የሥራ ፈጣሪዎች የማበረታታት ዕድል አለው።

በተጨማሪም በስታርት አፑ ዘርፍ የሚሰማሩ አካላትም የባለቤትነት መብቱ አግኝተው በፍጥነት የፋይናንስ ድጋፍ የሚያገኙበት ዕድል መመቻቸቱን ያብራራሉ።

እንደ አቶ ወልዱ ገለጻ፤ በዓለም አቀፍ ደረጃ ከፍተኛ ኢኮኖሚ የገነቡ ሀገራት በአዕምሯዊ ንብረት ምዝገባቸው ከፍተኛ ደረጃ የደረሱ ናቸው። በተፈጥሮ ሀብት ብቻ በዓለም አቀፍ ኢኮኖሚ መወዳደር አይቻልም፤ የአዕምሯዊ ንብረት በማይዳሰስ ሀብት ውስጥ ሆኖ ከፍተኛ ልዩነት እየፈጠረ ያለ ዘርፍ ነው።

መንግሥት ጀማሪ ሥራ ፈጣሪዎችን /ስታርት አፖችን/ በተሻለ ሕግና የአሠራር ሥርዓት ለመደገፍ በልዩ ትኩረት እየሠራ መሆኑን ጠቅላይ ሚኒስትር ዐቢይ አሕመድ (ዶ/ር) የገለጹት የ"ስታርት አፕ ኢትዮጵያ" ፎረም በዓድዋ ድል መታሰቢያ መጋቢት ወር ላይ በተካሄደበት ወቅት ነው።

በወቅቱም የአይሲቲ ዘርፍ ከአምስቱ የብዝኃ ኢኮኖሚ አዕማዶች አንዱ ሆኖ በትኩረት እንዲሠራበት መደረጉ ጀማሪ ሥራ ፈጣሪዎችን /ስታርት አፖችን/ ለማበረታታት የተወሰደ እርምጃ ማሳያ መሆኑን መግለጻቸው የሚታወስ ነው። ከለውጡ በፊት በሀገር አቀፍ ደረጃ ያሉ ስታርት አፖች ከ50 እንደማይበልጡ ጠቅሰው፣ አሁን ላይ ከ900 በላይ ስታርት አፖች መኖራቸውን ነው የተናገሩት።

# የሚኒስትሮች ምክር...

**ከ1ኛ ገጽ የዞረ**

በሰፊው ከተወያየበት በኋላ በሥራ ላይ እንዲውል በሙሉ ድምፅ መወሰኑ ታውቋል።

በመቀጠል ምክር ቤቱ የተወያየው በፌዴራል መንግሥት የተጨማሪ በጀትና የወጪ አሸፋፈን ማስተካከያ አዋጅ ላይ ነው። ይህ የማስተካከያ አዋጅም የተጨማሪ በጀትና የወጪ አሸፋፈን ማስተካከያው የተሻሻለውን የ2017-2021 የመካከለኛ ዘመን የማክሮ ኢኮኖሚና ፊስካል ማሕቀፍ ማስፈጸም በሚያስችል መልኩ የመንግሥት የፋይናንስ አቅምና ተጠባቂ ገቢዎችን ታሳቢ በማድረግ፣ የተጨማሪ በጀት ታሳቢዎችንና የወጭ ታሳቢዎችን ግምት ውስጥ በማስገባት መዘጋጀቱን ተጠቅሷል።

በዚሁ መሠረት ለመደበኛ ወጪዎችና የወጪ አሸፋፈን ለማስተካከል የሚውል 581,982,390,117 / አምስት መቶ ሰማንያ አንድ ቢሊዮን ዘጠኝ መቶ ሰማንያ ሁለት ሚሊዮን ሶስት መቶ ዘጠና ሺህ አንድ መቶ አስራ ሰባት ብር/ ተጨማሪ በጀት ለምክር ቤቱ ቀርቧል። ምክር ቤቱም በቀረበው የፌዴራል መንግሥት የ2017 በጀት ዓመት የተጨማሪ በጀትና የወጪ ማስተካከያ ረቂቅ አዋጅ ላይ ከተወያየ በኋላ ግብዓቶችን በማከል ወደ ሕዝብ ተወካዮች ምክር ቤት እንዲተላለፍ በሙሉ ድምፅ ወስኗል።

በሦስተኛ ደረጃ የተወያየው በኢትዮጵያ የተመሰከረላቸው የሂሣብ ባለሙያዎች ኢንስቲትዩት ማቋቋሚያ ረቂቅ አዋጅ ላይ ነው። ምክር ቤቱም በረቂቅ አዋጁ ላይ በሰፊው ከተወያየበት በኋላ ግብዓቶችን በማከል ለሕዝብ ተወካዮች ምክር ቤት እንዲተላለፍ በሙሉ ድምፅ ወስኗል።

የደረቅ ቆሻሻ አያያዝና አወጋገድ ረቂቅ አዋጅ ሌላው ምክር ቤቱ የተወያየበት አጀንዳ ነው። ደረቅ ቆሻሻ በአካባቢ እና በሰዎች ደኅንነትና ጤና ላይ እያስከተለ ያለውን ተፅዕኖ እና ጉዳት ለመከላከልና ለመቆጣጠር ምክር ቤቱም በአዋጁ ላይ በሰፊው ከተወያየ በኋላ ለሕዝብ ተወካዮች ምክር ቤት እንዲተላለፍ በሙሉ ድምፅ ወስኗል።

ሌላው ምክር ቤቱ የተወያየው የብሔራዊ ተሐድሶ ኮሚሽን ማቋቋሚያ ደንብን ለማሻሻል በወጣ ደንብ ላይ ነው። ተቋሙ በሕግ የተሰጠውን ተግባርና ኃላፊነት መወጣት እንዲችል ማቋቋሚያ ደንቡን ማሻሻል አስፈላጊ ሆኖ በመገኘቱ ደንቡ ተዘጋጅቶ ለምክር ቤቱ ቀርቧል። ምክር ቤቱም በደንቡ ላይ በሰፊው ከተወያየ በኋላ በፌዴራል ነጋሪት ጋዜጣ ታትሞ ከወጣበት ቀን ጀምሮ ተግባራዊ እንዲደረግ በሙሉ ድምፅ ወስኗል።

የውሃ አካል ዳርቻ አከላለል፣ ልማት፣ እንክብካቤና አጠቃቀም ረቂቅ አዋጅ ላይ ምክር ቤቱ የተወያየበት ስድስት አጀንዳ ነው። የውሃ አካላት ዳርቻ መከለልና በዘላቂነት ማልማት፣ መንከባከብና ጥበቃ ማድረግ የውሃ ሥነ-ምሕዳር አገልግሎትን ከማሻሻል ባሻገር ለአካባቢው ማኅበረሰብ ተጨማሪ ማኅበራዊና ኢኮኖሚያዊ ጥቅሞችን የሚያስገኝ በመሆኑ አዋጁ ተዘጋጅቶ ለምክር ቤቱ ቀርቧል። ምክር ቤቱም በአዋጁ ላይ በሰፊው ከተወያየ በኋላ ለሕዝብ ተወካዮች ምክር ቤት እንዲተላለፍ በሙሉ ድምፅ ወስኗል።

ሌላው ምክር ቤቱ የተወያየበት አጀንዳ የተቀናጀ ውሃ ሀብት አስተዳደር ማስፈጸሚያ የተፋሰሶች ከፍተኛ ምክር ቤት ማቋቋሚያ ረቂቅ አዋጅ ላይ ነው። የተቀናጀ ውሃ ሀብት አስተዳደርን በተፋሰስ ደረጃ ተግባራዊ በማድረግ ስትራቴጂካዊ አመራር መስጠት አስፈላጊ በመሆኑ ረቂቅ አዋጁ ተዘጋጅቶ ለምክር ቤቱ ቀርቧል። ምክር ቤቱም በአዋጁ ላይ በሰፊው ከተወያየ በኋላ ግብዓቶችን በማከል ለሕዝብ ተወካዮች ምክር ቤት እንዲተላለፍ በሙሉ ድምፅ መወሰኑን የጠቅላይ ሚኒስትር ጽሕፈት ቤት መረጃ አመልክቷል።

# ሙዝን በችርቻሮ ከመሸጥ...

**ከ1ኛ ገጽ የዞረ**

ያይኔአበባ ከልጅነቷ ጀምሮ ሥራ ወዳድና ለመለወጥ ጽኑ ፍላጎት ነበራት። አንድ ቀን የራሷን ሥራ ከፍታ ለበርካቶች የሥራ ዕድል እንደምትፈጥር ቅንጣት ያህል ጥርጣሬ አልነበራትም። ይህን ሕልሟን እውን ለማድረግ የአርሶ አደር ማሳን በመከራየት የሙዝ ልማት ሥራ ጀመረች። ይህም ቢሆን በምትፈልገው ልክ ለውጥ ሊያመጣላት ባለመቻሉ ሥራ እንደምትወድና ዕድሉ ቢሰጣት በአጭር ጊዜ ውስጥ እንደምትለወጥ ለክልሉ የኢንቨስትመንት ቢሮ ተማፅኖዋን አሰማች። ጥረቷን የሚያውቁት አመራሮች ጥያቄዋን ተቀብለው፤ በአርባ ምንጭ ከተማ ዙሪያ 10 ሺህ ሄክታር መሬት እንድታገኝ አደረጉ። ዛሬ ላይ ባለሀብት ሆናለች፤ ወደፊትም ብዙ ሕልሞች አሏት።

ያይኔአበባ አስፋው ለኢትዮጵያ ፕሬስ ድርጅት እንደገለጸችው፤ የሥራ ፍላጎቴን በመመልከት የጋሞ ዞን የኢንቨስትመንት መምሪያ 10 ሺህ ሄክታር የኢንቨስትመንት ቦታ ሰጥቶኛል። በ10 ሺህ ሄክታር መሬት ላይ ቀደም ሲል ቲማቲም በማምረት ተጠቃሚ መሆን ችያለሁ። አሁን ላይ የሙዝና ሀባብ ምርት በስፋት አመርታለሁ። ቀደም ሲል ቲማቲም በ10 ሄክታር መሬት ላይ በማልማት እስከ ቶጎጫሌ በመላክ እስከ 32 ሚሊዮን ብር ገቢ ማግኘቷን ገልጻለች። በአሁኑ ጊዜም በድምሩ 40 ሚሊዮን ብር ካፒታል አስመዝግባለች።

የቅዳሜና እሁድ ገበያዎች ላይ ምርቷን በማቅረብ ለዋጋ መረጋጋት የበኩሏን አስተዋፅዖ መወጣቷን ገልጻለች። የማለማው የሙዝ ዝርያ የተዳቀለው በመሆኑ ውጤታማ ነው ትላለች።

ቀደም ሲል በመንገድ ላይ ሙዝና ማንጎ ትሸጥ እንደነበር የምታስታውሰው ያይኔ አበባ፤ ሙዝና ማንጎን ለመንገደኞች በመሸጥ የዕለት ጉርስን ለማግኘት ትግል ነበር። ነገር ግን ባለፉት አምስት ዓመታት የኢንቨስትመንት ቦታ በማግኘቴ ከፍተኛ ገቢ እያገኘሁ ነው። የኑሮ ደረጃዬ በሚገባ ተሻሽሏል። ቀደም ሲል ተከራይቼ ነበር የምኖረው፤ አሁን ዘመናዊ ቪላ ቤት ገንብቻለሁ። እንዲሁም በአርባ ምንጭ ከተማ አራት ቦታዎችን አፍርታለች። ለማረስ፤ መከስከሻና ቦይ ለማውጣት አገልግሎት የሚውል የግሏ ትራክተር አላት። ምርቷን ለማጓጓዝ ሲኖትራክ መኪና ገዝታለች።

ሥራ ከጀመረችበት ጊዜ አንስቶ ለበርካታ ቋሚና ጊዜያዊ ሠራተኞች የሥራ ዕድል የፈጠረችው አልሚዋ፤ አሁን ላይ 62 ቋሚና ጊዜያዊ ሠራተኞች አሏት። ከእነዚህ ውስጥ 12ቱ በግብርና የተመረቁ ናቸው። ከዚህ ቀደም ግብርና የወንድ እንጂ የሴት ነው የሚል አስተሳሰብ ባለመኖሩ በዘርፉ ብዙ ሴቶች ሲሰማሩ አይስተዋሉም። ነገር ግን ከለውጡ ወዲህ ለሴቶች በተሰጠው ትኩረት ብዙ ሴቶች በግብርናው መስክ በመሰማራት እራሳቸውን ከኢኮኖሚያዊ ጥገኝነት በማላቀቅ ለብዙዎች የሥራ ዕድል እየፈጠሩ ነው ስትል ትገልፃለች።

ከባዱ ሥራ ግብርና ነው የምትለው በግብርና ተሰማርታ ውጤታማ የሆነችው ያይኔአበባ፤ ለሁሉም ሥራ ብርታትና ሥራ ወዳድነት መሠረታዊ ነው። ከሙዝ በተጨማሪ በብዛት ቲማቲም፣ ሽንኩርት፣ ቃሪያና የአበሻ ጎመን አመርታለሁ። በቀን ውስጥ ለመሥራት ያሰብኩትን ሳላሳካ ወደ ቤት አልገባም፤ የእርሻ ልማቴን ለአፍታም ቢሆን አልነጠለውም። እስከ ምሽት ስድስት ሰዓት ድረስ በሥራ የማሳልፍበት ጊዜ አለ። ሴቶች ከኢኮኖሚ ጥገኝነት ለመውጣት ጠንክረው መሥራት እንዳለባቸውም ትመክራለች።

ሴቶች የራሳቸውን ሥራ እንዲጀምሩ ድጋፍ እያደረኩ ነው የምትለው ያይኔአበባ፤ ተቀጥረው ለሚሠሩ ሴቶች የሙዝ ችግኝ እየሰጠሁ ነው። ወደፊት ከቅጥር ሥራ ተላቀው የራሳቸው የሙዝ ልማት እንዲኖራቸው ለማድረግ ምክር ጭምር እሰጣለሁ። ለአርሶ አደሮች የተዳቀለውን የሙዝ ዝርያ በመስጠት ማኅበራዊ ኃላፊነቴን እየተወጣሁ ነው ስትል ትገልጻለች።

የተዳቀለው የሙዝ ዝርያ በአጭር ጊዜ ውስጥ ለገበያ መቅረብ ይችላል። እንዲሁም ምርታማ ነው፣ ሥራው እንደሌሎች የሙዝ ዝርያዎች አድካሚ አይደለም። ውሃን ለረጅም ጊዜ የመያዝ አቅም ስላለው ድርቅን እንደሚቋቋም ገልጻለች። ወደፊት በአርባ ምንጭ ከተማ ትልቅ የገበያ ሞል የመገንባት እቅድ አለኝ፤ አሁን ላይ ለክልሉ መንግሥት ጥያቄዬን አቅርቤያለሁ ብላለች።

ማህበራዊ

# ወጣቶች





ወጣት ኒቆዲሞስ የሺጥላ የእንደራሴ ወጣቶች ማኅበር ጠቅላይ ጸሀፊ

## የወጣቶች እንደራሴ ...

**ሰሚራ በርሀ**

‹‹እንደራሴ ማለት በድሮ ጊዜ ወይንም ስልጣኔ የሚባለውን እሳቤ ከመቀበላችን በፊት ሀገሩን ወክሎ በተለያዩ ቦታዎች ላይ የሚዘዋወር ሰው እንደራሴ ይባል ነበር። አሁን ላይ አምባሳደር በመባል በተለያዩ ሀገራት እንደሚሾሙት ማለት ነው።›› በማለት ስያሜውን ያብራራል። ወጣት ኒቆዲሞስ የሺጥላ፡፡

ወጣት ኒቆዲሞስ የእንደራሴ የወጣቶች ማኅበር ጠቅላይ ጸሀፊ ነው። ማኅበሩም በሚንቀሳቀስባቸው ቦታዎች እና በሚሳተፍባቸው መድረኮች የወጣቶች እንደራሴ ወይንም አምባሳደር መሆንን ዓላማው አድርጎ እየሰራ ይገኛል። ይህ የወጣቶች ማኅበር ዓላማው ለወጣቶች የተለያዩ እድሎችን በመስጠት ማብቃት ዓላማው ያደረገ መሆኑን ወጣት ኒቆዲሞስ ይገልጻል ።

እንደራሴ የወጣቶች ማኅበር ከተመሰረተ ሶስት ዓመት ያክል ጊዜን አስቆጥሯል። የሲቪል ማኅበረሰብ ምዝገባ ፍቃድ ያገኘው ይህ የወጣቶች ማኅበር የተመሰረተው በአንድ ወጣት አማካኝነት ነው። የማኅበሩ መስራች ወጣት ብሩክ አስቻለው ዓላማ እና ሀሳብ የሚጋሩ በርካታ ወጣቶች በአባልነት እና በበጎፍቃደኝነት ማኅበሩን በመቀላቀል ማኅበሩ በሚያከናውናቸው የተለያዩ ተግባራት ላይ በማሳተፍ ላይ ይገኛል።

ወጣቶችን በተለያየ መንገድ ለማብቃት የተለያዩ ስልጠናዎችን በመስጠት ያላቸውን እውቀት በልምድ እንዲያዳብሩ የስራ እድሎችን በመስጠት ወጣቶች ላይ ይሰራል። ‹‹ ሲመሰረት በአንድ ሰው የተመሰረተ ቢሆንም ዓላማው ጠንካራ ስለነበር ሌሎች በዚህ ዓላማ የምናምን ወጣቶችን ስቦን በጋራ እየሰራን እንገናኛለን። ›› ሲል ወጣት ኒቆዲሞስ ማኅበሩ ለወጣቶች የሚሰጣቸውን ጥቅሞች ያስረዳል ።

‹‹ እንደራሴ በዋናነት ሶስት ዓላማ አለው። አንደኛው ለወጣቱ ዓላማ መስጠት ራሳቸውን እንዲያውቁ ማድረግ ነው። ሁለተኛው ዓላማቸውን ግባቸውን እንዲያሳኩ የተለያዩ እድሎችን መስጠት ስልጠናዎችን ማዘጋጀት፣ ሶስተኛው ከራሳቸው አልፈው ማኅበረሰባቸውን እና ሀገራቸውን የሚረዱ ወጣቶች ማድረግ ነው። ››

ወጣቶችን በማብቃት እና እድል በመስጠት ወጣቶች ባላቸው እውቀት የተሻለ እንዲሆኑ የሚሰራው ይህ ማኅበር አፍሪካ ወጣቶች ፎረም በኢትዮጵያ ለመጀመሪያ ጊዜ እንዲካሄድ አስችሏል። ‹‹ የአፍሪካ የወጣቶች ፎረም አኅጉር አቀፍ ነው። እንደአኅጉርም በኢትዮጵያ ሲዘጋጅ ለመጀመሪያ ጊዜ ነው።›› የሚለው ጠቅላይ ጸሀፊው በቀጣይም በኢትዮጵያ የተለያዩ ሀሳቦች እና መድረኮች እንደሚቀጥል ጠቁሟል ።

የአፍሪካ ወጣቶች ፎረም በኢትዮጵያ ሲዘጋጅ ‹‹ በአፍሪካ ሰለብሬትስ›› ወይንም አፍሪካ ታከብራለች በተሰኘው የባሕል፤ የፋሽን እና የቢዝነስ ሳምንት ውስጥ ነው። በዚህ ሁነት ውስጥ የአፍሪካ ወጣቶች ፎረም ራሱን ችሎ ሲዘጋጅ ይህ የመጀመሪያው ነበር። የእንደራሴ ወጣቶች ማኅበር ይህንን እድል ለማግኘት እና ፎረሙን ለመጀመሪያ ጊዜ በኢትዮጵያ እንዲዘጋጅ ለማድረግ ትልቅ ጥረት ማድረጉን ጠቅሷል።

‹‹ እንደራሴ በወጣቶች የሚመራ እና ወጣቶች ላይ የሚሰራ ድርጅት ነው። ›› በማለት የሚገልጸው የማኅበሩ ጠቅላይ ጸሀፊ እንደራሴ በዙሪያው ያሉ የተለያዩ ወጣቶችን ለማብቃት በሚሰራቸው ስራዎች ውስጥ ከተለያዩ ሀገር ውስጥ ከሚገኙ የወጣት ማኅበራት እና ቡድኖች ጋር እንዲሁም በአኅጉረ አፍሪካ የሚገኙ ትልልቅ ተቋማት ጋር በመቀናጀት ኢትዮጵያውያን ወጣቶች የሚጠቀሙበትን እድል ለመፍጠር የሚሰራቸው ስራዎች ለዚህ ፎረም አዘጋጅነት እንዲመረጥ አድርገውታል ።

‹‹ ወጣቶች ለአፍሪካም ሆነ ለኢትዮጵያ መፍትሄ ናቸው ብለን ነው የምናምነው። አኅጉራችን ባሏት የወጣቶች ቁጥር ሁለተኛ ደረጃ ላይ ነው የምትገኘው። ተፈጥሯዊ ሀብት፣ የሰው ኃይል ኖሮን ነገር ግን እድገት ማምጣት ያልቻልነው ወጣቱን መጠቀም ስላልቻልን ነው። ›› ይህንን የወጣት ቁጥር ወደ ሀብት በመቀየር ለአፍሪካ ወደፊት መራመድ ምክንያት መሆን የማኅበሩ ዓላማ ነው ።

የዘንድሮው ዓመት ‹‹አፍሪካ ታከብራለች ›› ክንውን በተባበሩት መንግስታት የአፍሪካ ኢኮኖሚክ ኮሚሽን ውስጥ ተካሂዷል። ክንውኑ ለሶስት ቀናት የቆየ ሲሆን ለሶስት ቀን የቆየ የፋሽን ኤግዚቢሽን፣ የባሕል ምሽት እንዲሁም በአፍሪካ ወጣቶች ፎረም አልፏል። እ.አ.አ 2024 ከሕዳር ስድስት እስከ ስምንት ለሶስት ቀናት በቆየው የአፍሪካ ታከብራለች ክንውን ውስጥ በመካተት የአፍሪካ ወጣቶች ፎረም ለመጀመሪያ ጊዜ በኢትዮጵያ ሊካሄድ ችሏል ፡፡

‹‹ አፍሪካን ሰለብሬትስ ከዚህ በፊት በኢትዮጵያም ሆነ በሌሎች የአፍሪካ ሀገራት ይዘጋጃል። የወጣቶች ፎረምን አካቶ ሲዘጋጅ ግን በኢትዮጵያ የመጀመሪያው ነው። ›› በማለት የሚያብራራው ጸሀፊው ይህንን ለማሳካት ማኅበሩ በሀገር ውስጥ እና በሌሎች የአፍሪካ ሀገራት ላይ ከሚገኙ ወጣት ማኅበራት ጋር የሚያደርጋቸው ግንኙነቶች፣ የልምድ ልውውጦች ፎረሙን ለማዘጋጀት እንዲመረጥ ምክንያት እንደሆነው አስታውሷል።

የአፍሪካ ታከብራለች ክንውን ዋና ዓላማውም የበለጸገች አፍሪካን እውን ለማድረግ በአፍሪካ የበለጸገ የጥበብ፣ የባህል፣ የቅርስ፣ የንግድ እና የኢንቨስትመንት የሳይንስ እና ቴክኖሎጂ ሽግግርን በማስተዋወቅ የአፍሪካን ኢኮኖሚያዊ፣ ማኅበራዊ እና ፖለቲካዊ ውህደት በማበረታታት የአፍሪካን በልዩነት ውስጥ ያለውን አንድነት ማክበር ነው።

በአፍሪካ ወጣቶች ፎረም ላይ በተለያዩ የሀገሪቱ ክፍሎች የሚገኙ ወጣቶች ተሳትፈዋል። በስራ ላይ የሚገኙ፣ የከፍተኛ ትምህርት ተቋማት ተማሪዎች ወጣቶች በፎረሙ ላይ ተሳትፈዋል። በፎረሙ አፍሪካ በተባበሩት መንግስታት ቋሚ መቀመጫ እንደሚገባት ተነስቷል።

በፎረሙ ላይ ወጣት ስራ ፈጣሪዎች ልምዳቸውን አጋርተዋል። ተሳታፊ ከነበሩ ወጣቶች ጋር እንዲሁ የስራ ፈጠራ እንቅስቃሴን እና ትምህርት በአፍሪካ እና በኢትዮጵያ ምን ይመስላል በሚል ርዕስ የፓናል ውይይት ተዘጋጅቷል። ስለ ስራ ፈጠራ፣ ወጣቶች በቢዝነስ ዙሪያ ሊኖራቸው ስለሚገባ እውቀት፣ በቢዝነስ ዓለም ስለሚገጥሟቸው ፈተናዎች እና መፍትሄዎች በውይይት ላይ የተነሱ ሀሳቦች ናቸው።

**የአፍሪካ ወጣቶች ፎረም በኢትዮጵያ ሲዘጋጅ ‹‹በአፍሪካ ሰለብሬትስ›› ወይንም አፍሪካ ታከብራለች በተሰኘው የባሕል፤ የፋሽን እና የቢዝነስ ሳምንት ውስጥ ነው**

ወጣቶች አሁን ዓለም እያስተናገደች ባለችው ፈጣን ለውጥ ውስጥ አብረው መጓዝ የሚችሉ መሆን እንደሚገባቸው በመድረኩ ላይ ተገልጿል። ራሳቸውን በእውቀት ማብቃት፣ ከቀለም እውቀት ባሻገር ባህሪያቸው፣ ከሌሎች ጋር በጥምረት የመስራት፣ የስራ - ስነምግር፣ ከሰዎች ጋር የመግባባት፣ ያላቸውን አቅም የመግለጽ የስነ-ተግባቦት ክህሎቶቻቸው ላይ መስራት እንደሚገባቸው በፓናል ውይይቱ ላይ ተነስቷል።

በአፍሪካ ያሉ ሀገራት ምንም እንኳን የተለያዩ ቢሆኑም ተመሳሳይ የሆነ ችግርን እንደሚያስተናግዱ በመድረኩ ላይ ተነስቷል። የፓን አፍሪካን እሳቤን በማምጣት በአፍሪካ የሚገኙ ወጣቶች በጋራ መስራት እንደሚገባቸውም ተጠቁሟል። በኢትዮጵያ የራሳቸው የሆነ ራዕይ ያላቸው በርካታ ወጣቶች አሉ። የሚገጥሟቸውን ፈተናዎች ወደ እድል በመቀየር የመፍትሄ አካል መሆን እንደሚችሉ ተጠቁሟል። ወደ ስራ ፈጠራ የሚገቡ ወጣቶችን ለመደገፍ የሚያስችል ምቹ ስነ-ምሕዳር መፍጠር ከሚመለከታቸው አካላት የሚጠበቅ መሆኑም በፓናሉ ላይ ከተነሱ የመፍትሄ ሀሳቦች ውስጥ ነው።

በዚህ ክንውን ውስጥ የተካሄደው በፓናል ውይይት ላይ ልምዱን ለማጋራት የተገኘው የሀሁ ጆብስ የስራፈጣሪ ኦፐሬሽናል ዳይሬክተር ናትናኤል ታምራት የአፍሪካ ወጣቶች ፎረም በአፍሪካ ኢኮኖሚክ ኮሚሽን ጊቢ ውስጥ በትልቁ የአፍሪካ አዳራሽ ውስጥ መካሄዱ ለየት እንደሚያደርገውም ገልጿል። ወጣቶችን ያሳተፈው የአፍሪካ ወጣቶች ፎረም እንደ አኅጉርም ሆነ እንደ ኢትዮጵያ ትልቅ ትርጉም በሚሰጠው እና ግርማዊ ቀዳማዊ ኃይለስላሴ ጥር 29 ቀን 1953 ዓ.ም ለአፍሪካውያን ሕዝብ የወደፊት እድገት መታሰቢያ ይሆን ዘንድ መርቀው በከፈቱት የአፍሪካ አዳራሽ መካሄዱ ለየት ያደርገዋል። ‹‹ ወጣቶች ስራ ፈጠራ ላይ እና ቢዝነስ ተኮር የሆኑ እንደዚህ አይነት መድረኮችን ማግኘታቸው በጣም ጥሩ እድል ነው። ›› ሲልም ናትናኤል አክሏል።

የእንደራሴ የወጣቶች ማኅበር የተመሰረተው በአዲስ አበባ ውስጥ ቢሆንም ሌሎች በየሀገሪቱ ክፍሎች ላይ የሚገኙ ወጣቶችን በማሳተፍ ምን ስራዎችን እየሰራ ነው ብለን ጥያቄ አቅርበንለታል። ‹‹ በማኅበራችን ውስጥ በርካታ በጎፍቃደኞችን እናሳትፋለን በዚህም በአካልም ባንሄድ በሀዋሳ፣ ድሬዳዋ፣ ጅግጅጋ የሚገኙ ወጣቶች የተለያዩ ወጣቶች የሚገናኙባቸውን መድረኮች ፈጥረው ይሰራሉ። ››

ማኅበሩ ከሚሰራቸው ስራዎች ውስጥ ለወጣቶች በተለያዩ ርዕሶች ላይ ያተኮሩ ስልጠናዎችን ይሰጣል። ከዩኔስኮ ጋር በነበረው የሁለት ዓመት ስምምነት በተለያዩ የሀገሪቱ ክፍሎች ላይ የሚገኙ ወጣቶችን በማሰባሰብ ስልጠና እንዲሰጥ አድርጓል። ‹‹ እርግጥ ነው አዲስ አበባ ውስጥ በርካታ ወጣቶችን ማግኘት ችለናል። የዚህ ዓመት እቅዳችንም በሌሎች የሀገሪቱ ክፍሎች የሚገኙ ወጣቶች ጋር መድረስ እንፈልጋለን። ›› የኒቆዲሞስ ሀሳብ ነው።

ወጣት ኒቆዲሞስ ያጠናው Global studies and International Relations) የእንደራሴ ወጣት ማኅበር ለመቀላቀል አስቀድሞ ስለማኅበሩ ይሰማው የነበረ መረጃ ቀርቦ አባል እንዲሆን አድርጎታል። ‹‹መጀመሪያ እንደራሴን ስቀላቀል የኮሙኒኬሽን ባለሙያ በመሆን ማኅበሩን ለማገልገል ነበር ። ›› በማለት ጊዜውን የሚያስታውሰው ወጣት ኒቆዲሞስ ማኅበሩ የሚሰራበት ዓላማ እና በማኅበሩ ውስጥ የነበረው ሚና አድጎ በቋሚነት ማኅበሩን በመቀላቀል አሁን እየሰራበት ወደሚገኘው የጠቅላይ ጸሀፊ ስራ ላይ ይገኛል ። በማኅበሩ ውስጥ በበጎ ፍቃድ አገልግሎት ለመሳተፍ ገደብ የሌለው ሲሆን በዓለም አቀፍ ግንኙነት፣ በፖለቲካ ሳይንስ እና የኮምፒውተር ሳይንስ እና በሌሎች የሙያ ዘርፎች ላይ የሚገኙ ወጣቶች ይገኙበታል።

ወጣቶች በተለያየ መንገድ ማኅበሩን በበጎፍቃደኛነት የሚቀላቀሉ ሲሆን፤ በበጎፍቃደኝነት ለተሳተፉ አባላት የተለያዩ በማኅበሩ በኩል የሚመጡ እድሎችን ስልጠናዎችን እንዲያገኙ እድል ይሰጣል። ‹‹ በእንደራሴ በኩል ከበርካታ ተቋማት ጋር የመስራት እድል አለን። እነዚህ ተቋማት ሰራተኞችን አሰልጥነው መቅጠር ፈልገው ወደ እኛ ሲመጡ በማኅበራችን የበጎፍቃድ አገልግሎት ተሳታፊዎችን ቅድሚያ እንሰጣለን፡፡››

ከተመሰረተ ሶስት ዓመት የሆነው የእንደራሴ የወጣቶች ማኅበር ወደፊት በሀገር ውስጥ የተመሰረተ ዓለምአቀፍ ተቋም በማድረግ ከአፍሪካ ውጪ በመስራት ወጣቶችን ማገናኘት በእቅዶቹ ውስጥ የተያዘ ነው።

## የምድር በረከት

# የወርቅ ምርትን በእጥፍ የሚያሳድገው ‹‹ኢትኖማይኒንግ›› ፋብሪካ

**ወርቅነሽ ደምሰው**

ኢትዮጵያ በወርቅ ማዕድን ሀብቷ ትታወቃለች፤ ይህን ማዕድን አልምቶ ተጠቃሚ መሆን ላይ ግን ብዙም አልተሰራባትም። ለእዚህ አንዱ ምክንያት ልማቱ እየተካሄደ ያለው በባሕላዊ መንገድ መሆኑ ነው። ወርቅ በአብዛኛው ሲመረት የኖረውም ሆነ እየተመረተ ያለው በእዚሁ በባሕላዊ መንገድ መሆኑ ይታወቃል።

ወርቅ ከባሕላዊ የአመራረት ዘዴ አለመላቀቁ ዜጎችም ሀገሪቱም ከእዚህ ወድ ሀብት የሚገባቸውን ያህል ተጠቃሚ እንዳይሆኑ አርጓቸው ኖሯል። ይህ ባሕላዊ አመራረት የወርቅ ሀብት እንዲባክን ከማድረጉም ባሻገር ምርቱ ለሕገወጦች ሲሳይ እንዲውል ሲያደርገውም ነው የቆየው።

መንግሥት ይህ ሀብት እንዳይባክን ተገቢውን ጥቅም እንዲሰጥ ለማድረግ መስራት ውስጥ ከገባ ቆይቷል። የወርቅ ማዕድኑ በአግባቡ ለምቶ ለዜጎችና ለሀገር ተገቢውን ጥቅም እንዲሰጥ፣ ሀገሪቱ ለተያያዘችው ልማት የፋይናንስ አቅም እንዲሆን፣ ለዜጎች የስራ እድል እንዲያስገኝ ለማድረግ በትኩረት እየሰራ መሆኑ ነው፡፡

በባሕላዊ መንገድ የሚካሄደው የወርቅ ልማት እንዲዘምን ለማድረግ ስልጠናዎችን በመስጠት፣ ቴክኖሎጂዎችን በማቅረብ፣ ወጣቶች በማሕበር ተደራጅተው ወደ ልማቱ እንዲገቡ በማድረግ ተሰርቷል፤ እየተሰራም ነው። በዚህም ለአያሌ ዜጎች የስራ እድል መፍጠር ተችሏል፤ በባሕላዊ መንገድ የሚያለሙትን ማሽነሪ ካላቸው ጋር በማስተሳሰር ልማቱ እንዲዘመን ለማድረግ ጥረት እየተደረገ ይገኛል።

መንግስት ልማቱ ከዚህም በላቀ መልኩ እንዲካሄድ የወርቅ ልማቱን ለባለሀብቶች ክፍት አድርጓል። ይህን ተከትሎም ኩባንያዎች የወርቅ ማምረቻ ፋብሪካዎችን እየገነቡ ያሉበት ሁኔታ ይታያል። እነዚህ ኩባንያዎች ወደ ስራ ሲገቡ በባሕላዊ መንገድ ከወርቅ የሚገኘውን የወርቅ መጠን በብዙ እጥፍ እንደሚያሳድጉትም ታምኖበታል።

ከእነዚህ ፋብሪካዎች አንዱ የሆነውና በጋምቤላ ክልል ዲማ በሚባለው አካባቢ የተገነባው ‹‹ኢትኖ ማይኒንግ›› የወርቅ ማምረቻ ፋብሪካ አንዱ ሲሆን፣ የፋብሪካው ግንባታ ተጠናቆ ከትናንት በስቲያ በጠቅላይ ሚኒስትር ዶክተር ዐቢይ አሕመድ ተመርቋል።

ጠቅላይ ሚኒስትሩ በፋብሪካው ምርቃት ወቅት እንደተናገሩት፤ የዲማ ከተማ ከተመሰረተች ከ30 ዓመት በፊት ጀምሮ የወርቅ ግብይት ሲካሄድባት ቆይታለች። በአካባቢው የሚገኘው የወርቅ ማዕድን ለ30 ዓመታት ቢዛቅ ቢዛቅ ሊያልቅ አልተቻለም። ይህ የሚያመላክተው የጋምቤላ ክልል በተለይ ዲሞ በወርቅ ሀብት እጅግ ሀብታምና የደረጀ አካባቢ መሆኑን ነው፡፡

በአካባቢው ወርቅ በባሕላዊ መንገድ ሲወጣ የኖረ ሲሆን፣ እንዲህ አይነቱ የወርቅ ልማት አብዛኛው ወርቅ ለብክነት እንዲዳረግ በማድረግ ይታወቃል፤ የገበያ ሥርዓቱም ችግር ያለበት ከመሆኑ በተጨማሪ፣ ወርቅ የሚመረትበት መንገድ በራሱ ከአንድ ቶን የወርቅ አፈር ሊገኝ የሚገባውን ያህል ወርቅ እንዳይገኝ የሚያደርግ ነው። ‹‹ጥቂት አግኝተን አብዛኛው እንዲባክን የሚያደርግ አሰራር ነው›› ሲሉም ጠቅላይ ሚኒስትሩ አስታውቀዋል።

ኢትኖ ማይኒንግ በዲማ አካባቢ ሥራ መጀመሩ በአካባቢው ሲባክን የኖረውን ወርቅ በአጭር ጊዜ በከፍተኛ ጥራትና መጠን ለማምረት እንደሚያስችል ገልጸዋል። ይህ ፋብሪካ ይዞት የመጣው እድል በመጀመሪያ ደረጃ ለዲማ አካባቢ ባሕላዊ ወርቅ አምራቾች ከፍተኛ ፋይዳ እንዳለው አመልክተዋል።

አምራቾቹ እስከ አሁን እንደሚያደርጉት ወርቅ በጥቂቱ እያወጡ ገበያ ማውጣት ሳይሆን ያልተጣራውን የወርቅ ምርት ወደ ኩባንያ በማምጣት እንዲጣራላቸው ቢያደርጉ ቀደም ሲል ያገኙት ከነበረው ወርቅ በእጥፍ ሊያገኙ እንደሚችሉም ጠቁመዋል። የወርቅ ዝውውሩን ሕጋዊ ማድረግ የሚያስችል መሆኑም ሁለተኛው ፋይዳው መሆኑን ገልጸዋል። ዲማ ላይ የወርቅ ሽያጭ ሕገወጥ በሆነ መንገድ ሲሰራ ብዙ ጊዜ በሕይወት ላይ አደጋም ያጋጥማል ሲሉ ጠቅሰው፣ ባሕላዊ አምራቾቹ



ኢትኖማይኒንግ የወርቅ ፋብሪካ በኢትዮጵያ ብቻ ሳይሆን በአፍሪካ ደረጃም በዘመናዊነቱ የተመሰከረለት ነው

ወርቁን ወደፋብሪካው የሚያመጡ ከሆነ ብዙ ወርቅ ማግኘት ብቻ ሳይሆን ዝውውሩም ሕጋዊ ስለሚሆን ትርፋማ ይሆናሉ ብለዋል።

የዛሬ 31 እና 32 ዓመት ገደማ የአካባቢው ወርቅ አምራች ወርቁን ወደ ከተማ ወስዶ ከሸጠ በኋላ ብሩን እዚያው ጨርሶ ሳይጠቀም ይቀር እንደነበር ጠቅሰው፣ አሁን ወርቁ ወደዚህ ፋብሪካ መጥቶ እንዲጣራ ከተደረገ አምራቾቹም፣ ወረዳውም ሀገርም በከፍተኛ ሁኔታ ተጠቃሚ እንደሚሆኑ ገልጸዋል፡፡

‹‹በባሕላዊ መንገድ ወርቅ የምታመርቱ የዲማ አካባቢ ወርቅ አምራቾች የገበያ ማዕከላችሁ መሆን ያለበት ይሄ ፋብሪካ ነው›› ሲሉ ጠቅላይ ሚኒስትሩ አስገንዝበው፣ ፋብሪካው ይበልጥ ተጠቃሚ ስለሚያደርጋችሁ ሕገወጥ ከሆነው የግብይት ሥርዓት ወደዚህ ማምጣት ይኖርባችኋል›› ብለዋል።

ጠቅላይ ሚኒስትሩ እንዳሉት፤ ኢትኖ ማይኒንግ ይህንን ዘመናዊ ፋብሪካ ለመገንባት ሁለት ዓመት ተኩል ጊዜ ወስዶበታል። እንደዚህ አይነት ኢንቨስትመንት ለኢትዮጵያ የመጀመሪያው ነው። ፋብሪካው በውጭ የግሉ ዘርፍና በኢትዮጵያ ‹‹ሶቨርን ወርዝ›› በሚባል ድርጅት ትብብር የተሰራ ነው። በኢትዮጵያ ደረጃ በግሉ ዘርፍ እንደዚህ ያለ ዘመናዊ የወርቅ ፋብሪካ እስከዛሬ ኖሮ አያውቅም።

በሀገሪቱ ያሉት ፋብሪካዎች በሀገር ውስጥ ባለሀብቶችና በአብዛኛው በመንግስት ተጀምረው በኋላ ወደ ግሉ ዘርፍ የተሸጋገሩ ናቸው፤ ይሄኛው ከመነሻው ጀምሮ በግል ባለሀብት በግል ኢንቨስትመንት የተገነባ ፋብሪካ ነው።

ፋብሪከው በኢትዮጵያ ብቻ ሳይሆን በአፍሪካ ደረጃም በዘመናዊነቱ የተመሰከረለት /ሰርቲፋይድ የሆነ/ መሆኑንም ጠቅሰው፣ ከአንድ ቶን የወርቅ አፈር የምናመርተው የወርቅ መጠን በየትኛውም የአፍሪካ ሀገር ከሚመረተው ከፍ ያለ ነው›› ሲሉም የፋብሪካውን ዘመናዊነት ገልጸውታል።

ጠቅላይ ሚኒስትሩ እንዳስታወቁት፤ የዲማ አካባቢ በወርቅ ምርት፣ በወርቅ ሀብት በእጅጉ ይታወቃል። እንደዚህ አይነት ዘመናዊ ፋብሪካ በባሕላዊ አመራረት ወቅት ለብክነት ይጋለጥ የነበረውን በርካታ ወርቅ ከብክነት በመታደግ ለገበያ እንዲወጣ በማድረግ ያግዛል። ይህ ፋብሪካ ገና ስራ መጀመሩ ነው፤ አቅሙ ስላለው በጣም በአጭር ጊዜ ውስጥ በሁለትና ሦስት እጥፍ ማደግም ይችላል። ፋብሪካው እንዲያድግ ለማድረግ የገበያ ሥርዓቱ ሰላም የሰፈነበት መሆን ይኖርበታል፡፡

‹‹ቀደም ሲል ታደርጉ እንደነበረው ሁሉ የዲማ አካባቢ ነዋሪዎች ይህን ፋብሪካ እንደግል ሀብታችሁ መጠበቅ ይኖርባችኋል። ይህ ፋብሪካ ከሌለ ይባክን የነበረውን ወርቅ ማግኘት አይቻልም። በሀገር ደረጃ ባለው ጥቅም ብቻ ሳይሆን፣ እያንዳንዱ ሰው በተዘዋዋሪ ከዚህ ምርት ስለሚጠቀም ፋብሪካውን መጠበቅና እንዲሰፋ ማድረግ የሁላችንም የጋራ ሥራ መሆን አለበት›› ብለዋል፡፡

‹‹ሁላችሁም እንደምታውቁት ኢትዮጵያ በአፍሪካ ውስጥ ከፍተኛ የማዕድን ሀብት ያላት ሀገር ናት፤ ይህ ሀብቷ ግን ባክኗል›› ያሉት ጠቅላይ ሚኒስትሩ፣ የቅርብና የሩቅ ጠላቶቻችን እነዚህን ምርቶቻችን ከለሙ፣ ኢትዮጵያ ካደገች፤ ኢትዮጵያ ከተለወጠች ስጋት ትሆንብናለች ብለው ስለሚያስቡ ወርቁም፣ ታንታለሙም፣ አይርን ኦሩም፣ ሊትየሙም ሁሉም አይነት ማዕድናት ያላት ሀገር ምንም እንደሌላት ሆና እስካሁን ቆይታለች›› ብለዋል።

እሳቸው እንዳስታወቁት፤ ከለውጥ በኋላ መንግሥት የማዕድን ዘርፍ ከፍተኛ ትኩረት ከሚገባቸው ዘርፎች አንዱ ነው በማለት በሁሉም ዘርፍ ከፍተኛ እንቅስቃሴ ማድረግ ውስጥ ከገባ ቆይቷል። ‹‹ይህ ፋብሪካ የመጀመሪያችን እንጂ የመጨረሻችን አይደለም። በቅርቡ ተጨማሪ ፋብሪካዎችን እናስመርቃለን›› በማለት ገልጸዋል፡፡

ጠቅላይ ሚኒስትሩ እንደገለጹት፤ መንግስት ባለፉት ሁለትና ሦስት ዓመታት ከፍተኛ ሥራዎች ሲሰራ ቆይቷል፤ በዚህ ዓመት በኢትዮጵያ ታሪክ ለመጀመሪያ ጊዜ እስከ 2 ቢሊዮን ዶላር ከወርቅ ብቻ ለማግኘት ታቅዶ እየተሰራ ነው። ይህም ቢሆን ኢትዮጵያ ካላት አቅም አንጻር ሲታይ በጣም ውስን ነው።

‹‹በርትተን ብንሰራ፣ ለጠላት መሳሪያ ባንሆን፣ የማዕድን ሀብታችንን ብንጠቀም፣ ሰላማችንን ብንጠብቅ ኢትዮጵያ ለማኝ ሳትሆን ሰጪ፣ የተቸገረች ሳትሆን የበለጸገችና ሌሎችን የምትረዳ ስለምትሆን ሀብቶታችንን፣ የሰው ኃይላችንን፣ ጉልበታችንን መጠቀም ይገባናል›› ብለዋል፡፡

እሳቸው እንዳስታወቁት፤ ሰላም በራሱ አንድ ሀብት ነው፤ ሰላምን መጠበቅና ሀብታችንን ለልማት ማዋልና ወደ ሚጠቅም ነገር መመንዘር የመንግሥትም የሕዝብም የጋራ ኃላፊነት መሆኑን ተገንዝቦ መስራት ጠንክሮ መስራት ያስፈልጋል።

‹‹ይህ ጅማሮ ይቀጥላል፤ ጋምቤላ ይለማል፤ በሌሎች አካባቢዎች ያሉ ሀብቶች ሁሉ ይለማሉ፤ የኢትዮጵያን ብልጽግ እናረጋግጣለን›› ብለዋል። በግብርናም፣ በማዕድንም፣ በኢንዱስትሪም፣ በቱሪዝምና በቴክኖሎጂም ያሉን ሀብቶች ተስናስለው ሌሎች ዘርፎችን በማንቀሳቀስ የኢትዮጵያን ብልጽግና እውን እስኪያደርጉ ድረስ እንቅልፍ አይኖረንም ሲሉም አስገንዝበዋል። ለዚህ እንተባባር፣ እንበርታ፤ እንስራ ለለውጥና ለብልጽግና ለልማት በጋራ እንቁም›› ሲሉ መልዕክታቸውን አስተላልፈዋል።

መረጃዎች እንዳስታወቁት፤ ኢትኖ ማይኒንግ የአኮቦ



ጠቅላይ ሚኒስትር ዐቢይ አሕመድ (ዶ/ር)

ሚኒራልስ ኩባንያ መጋቢ ሲሆን፣ በስካንዲኔቪያን ሀገራት መሠረቱን ያደረገ በኢትዮድያ ኢንቨስትመንት ሆልዲንግስ በኩል ከኢትዮጵያ መንግሥት ጋር በወርቅ ፍለጋ እና ማውጣት ስራ ላይ የተሰማራ ኩባንያ ነው።

ፋብሪካው የተገነባበት የጋምቤላ ክልል ዲማ አካባቢ ከፍተኛ የወርቅ ሀብት ክምችት ያለበት ነው። ባለፉት ሶስት አስርት ዓመታት አካባቢው በአነስተኛና ባሕላዊ የወርቅ ማዕድን ማውጣት ስራ ትታወቃለች።

ፋብሪካው በአካባቢው በከፍተኛ ደረጃ ወርቅ ማምረት ኢንቨስትመንት ስራ ተሰማርቶ እየሰራ ይገኛል። በአጭር ጊዜ ውስጥ አመርቂ እና ደረጃውን የጠበቀ የወርቅ ምርት እንደሚያስገኝ ታምኖበታል፤ ለሕገወጥ ተግባር ተጋልጦ የቆየው የወርቅ ማዕድን በአግባቡ እንዲለማና ለገበያ እንዲቀርብ በማድረግ ተገቢውን ምላሽ እንደሚሰጥ ይጠበቃል።

ኢትኖ ማይንግ የማዕድን ፋብሪካ በኢትዮጵያም ሆነ በአፍሪካ ትልቅ ወርቅ አምራች ኩባንያ ነው። ፋብሪካው በሰዓት 10 ቶን የወርቅ አፈር የሚፈጭ ሲሆን፣ በዓመት ደግሞ አንድ ነጥብ አምስት ሚሊዮን ቶን አፈር ይፈጫል።

በእውቀትና ቴክኖሎጂ ሽግግር እስካሁን በሀገሪቱ ውስጥ ካሉ የማዕድን ፋብሪካዎች አዳዲስ ቴክኖሎጂዎችን በመጠቀም የሚስተካከለው እንደሌለም ተጠቁሟል። ይህ መሆኑ የአካባቢ ብክለት እና መሰል ተያያዥ ጥያቄዎችን የማያስነሳ ፋብሪካ እንዲሆን ያስችለዋል።

ለበርካታ ኢትዮጵያውያን የስራ እድል የፈጠረ ነው። ግንባታው እየተካሄደ ባለበት ወቅት ብቻ ለ220 ዜጎች ቋሚ የሥራ ዕድል ፈጥሯል። ወደ ሥራ ሲገባ ደግሞ ከዚህ በላቀ ደረጃ የሥራ ዕድል ይፈጥራል።

በአንድ ወቅት በጋምቤላ ክልል ዲማ ወረዳ ተገኝተን የግንባታውን ሂደት በተመለከትንበት ወቅት ያነጋገርናቸው የኢትኖ ማይንግ የወርቅ ፋብሪካ ሳይት ማናጀር ኢንጂነር ወልደገብርኤል አረጋዊ ክልሉ ትልቅ የወርቅ ሀብት ክምችት እንዳለው ጠቅሰው፣ ይህም በወርቅ ማዕድን ልማቱ ብዙ መሥራት እንደሚያስችል ገልጸው ነበር።

እሳቸው እንዳሉት፤ ፋብሪካው ልማቱን የሚያካሂደው በ16 ኪሎ ሜትር ስኩየር ቦታ ላይ ሲሆን፣ ይህም ፋብሪካው ያረፈበት እና ወርቅ ፍለጋው የሚከናወንበት ስፍራን ያካትታል። የማዕድን ጥሬ እቃ ወይም ወርቅ ያዘለ አለት የሚወጣበት ስፍራ በጣም ምቹ እና ትልቅ ሀብት ያለበት ነው። በአካባቢው ያለው ወርቅ ያዘለ አለት በጣም ከፍተኛ መሆኑን ጠቅሰው፣ ተፈላጊነቱም በዚያው ልክ መሆኑን ተናግረዋል።

በአካባቢው ከአንድ ቶን አፈር ውስጥ በአማካይ 22 ነጥብ 7 ግራም ወርቅ ማግኘት ይቻላል፤ የፋብሪካው በአካባቢው መገንባትም ይህን ሁሉ ታሳቢ አድርጓል። ለዚህም የሚውል ለየት ያለ ቴክኖሎጂ ሥራ ላይ ይውላል። የወርቅ ማዕድን አቅሙም ሆነ ያንን ለማውጣት የሚተከለው ፋብሪካ አቅም ለኩባንያው ብቻ ሳይሆን ለሀገሪቱ ከፍተኛ ፋይዳ አለው ሲሉ ተናግረዋል።

የቅርብ ጊዜ መረጃ እንዳመለከተው፤ በኢትዮጵያ በተደረገ የዳሰሳ ጥናት ከ517 ቶን በላይ የወርቅ ክምችት መኖሩ ተረጋግጧል።

መዝናኛ

# የብዕር ጠብታ

## የሚያስቁ ሳቆች

**በትረ ሙሴ (መልከ ኢትዮጵ)**

ወንድ አያቴ ጃጅቷል..ብቻውን እያወራ ብቻውን የሚስቅ ነው። ምን እንደሚል አይሰማኝም ግን ሁሌም ሲያወራ አየዋለሁ። ለመደመጥ የሚከብዱ፣ ለመሰማት ያልደረሱ ልጃገረድ ድምፆች ከአፉ በጆሮዬ ሽው ይላሉ..ሳልሰማቸው..ከአየሩ ጋር ይደባለቃሉ። ይሄ ብቻ አይደለም ጆሮውም ከድቶታል። ሹክሹክታ አይሰማም። አይደለም ሹክሹክታ እኔ ጆሮዬን የምይዝበትን ኃይለኛ ድምፅ እንኳን መስማት ይቸግረዋል። ጆሮው ላይ መጥተው ካላንባረቁበት በስተቀር ጆሮ ዳባ ነው። አለመስማት ብቻ አይደለም በመርሳትም የሚደርስበት የለም። ሦስት ሰዎችን ብቻ ነው የሚያስታውሰው። እኔን፣ አብራው ለሰባ ዓመት በትዳር የኖረችውን ሚስቱንና ከአልጋው በላይ የተሰቀለውን የሟች ወንድሙን ፎቶ። እኔን ያረሳኝ ሁሌ ነጋ ጠባ አጠገቡ ስለሚያገኘኝ ይመስለኛል። ሴት አያቴን ያረሳት ሰባ ዓመት ሙሉ ስለሚያውቃት ልርሳሽ ቢል ስለማይቻለው ይመስለኛል። አልጋው ላይ የተሰቀለውን የሟች ወንድሙን ፎቶ ያረሳው ከመጃጀቱ ሦስት ቀን ቀደም ብሎ የክርስቶስ ፎቶ እየመሰለው ሲሳለመው ነበር..ለዛ ይመስለኛል። እንደዛ ባይሆን ገና ድሮ ይረሳን ነበር። ሊጠይቁት በሳምንት ሦስት ጊዜ የሚመጡትን ያሳደጋቸውን ሁለት ወንድሞቼን እንኳን ረስቷቸዋል.. ከእጁ በልተው፣ ከእጁ ጠጥተው። በመጡ ቁጥር ፍጹምና አቤል ናቸው ብዬ ማስተዋወቅ የኔ ሥራ ነው።

ፊቱ ቆመው..እጃቸውን ለሰላምታ ዘርግተው ግራ ይገባዋል።

‹አቤልና ፍጹም ናቸው! እለዋለሁ ድምፄን አግንኜ። በዚህ ሁናቴ የልጅ ልጆቹን ለሁለት ዓመት እንደ አዲስ ተዋውቋቸዋል። ዘር አይውጣለትና እርጅና። አያቴ በመርሳት ተወዳዳሪ የለውም ያልኩት ለዚህ ነው። ዋሽሁ?

ሴት አያቴ ደግሞ ነገር አይገባትም። እንደ ወንድ አያቴ ሳትጃጅ፣ ጆሮዋ ሳይከዳት፣ በመርሳት ሳትጀግን ግን ነገር አይገባትም..ሙድ የላትም። በመደናገርና በማደናገር አንደኛ ናት። እሷን ከማስረዳት ከጆባይደን ቢሮ መረጃ መስረቅ ይቀላል። እንዲችው ልቤን እንዳወለቀችው መሽቶ ይነጋልኛል። ወላጆቼ በሕይወት ስለሌሉ በእነኚህ ሁለት ነፍሶች ተከብቤ የምኖር ነኝ። ምን እንደምመስል አይጠፋችሁም። ሁሌ እንደሳኩ..ሁሌ እንደተሳቀኩ ነው። ከወንድ አያቴ ሳመልጥ በሴት አያቴ ድንግርታ እደነቃቀፋለሁ..ግን ሳቆቼ ናቸው..በነፍሴ ላይ ብን የተደረጉ።

ዕጣ ክፍሌ አንድ ዓይነት ነው። ለማይሰማው አያቴ እየጮሁኩና ነገር በማይገባት ሴት አያቴ እየተደናበርኩ ወይም ደግሞ ጥርስ ለሌለው ድዳም አያቴ የተፈላውን አጥሚት እየኮመኮምኩ..በጠፍር የተሠራው ወንበር ላይ ቁጭ ብዬ። ወንድ አያቴ አልጋ ላይ ነው..ብቻውን እያወራ። ሴት አያቴ የትም ቦታ አለች..ዓለም ጠባት.. ምድር አንሳት። ለጎኗና ለዳናዋ በጠበበ ሰማይና ምድር ውስጥ ያለች ይመስለኛል..እንዴት ላለኝ የትም አያታለሁና። እንደ እኔና እንደ ወንድ አያቴ አንድ ቦታ የላትም። ትፈትላለች፣ ትደውራለች፣ ትንጣለች፣ ታልባለች፣ ኩበት ታኮብታለች፣ ዳቦ ትደፋለች፣ ታማለች፣ ቡና ስለማትጠጣ ቡና ብቻ ስታፈላ አላያትም። ሁሉንም ናት..

‹ዓለም ሊታለፍ ነው አሉ!› አልኩ አያቴ እንዲሰማኝ ድምፄን ከፍ አድርጌ። ሰሞኑን በዜና የሰማሁትን ሁላችንንም ያስገረመንን የአንዲትን እንስት ውሻ የማግባት ዜና አስታውሼ።

‹ማናት ዓለም? አለኝ አያቴ በሰለለና ብዙም በማይሰማ ድምፅ። ድምፄን ከፍ ስላደረኩ ሰምቶኛል። ደስ የሚለው ነገር አያቴ ከጮሁ ይሰማል።

እኔ ሳልመልስለት ሴት አያቴ ጣልቃ ገባች።

‹ያቺን የጎረቤታችንን ዘዋሪዋን ሴት ማለቱ ነዋ›። ስትል ከኔ ቀድማ ሴት አያቴ መልስ ሰጠች።

በደንብ ስላልጮኸች አያቴ መልስ አልሰጣትም። አያቴ ዝም አለ ማለት አልሰማም ማለት ነው። ሴት አያቴ ሁልጊዜ እየጮሁ ወንድ አያቴን ማስረዳት ሰልችቷታል መሰለኝ ብዙም አትጮህም። ለእኔ ተናግራ እኔ ጮኬ እንዳስረዳላት ነው የምትፈልገው። አሁን ግን ጮኬ ላስረዳላት አልፈለኩም ምክንያቱም እኔ ያልኩት ሌላ እሷ የምትለው ሌላ ነውና።

‹ታዲያ ትለፋ..ብታልፍስ ታዲያ? አለች አያቴ.. ወተቷን እየናጠች።

ወንድ አያቴ ባለመስማቱ ዝም ብሏል ሴት አያቴን ግን ማስረዳት ግዴታዬ ነው። ትክክት ባለው ሁናቴ ‹ኧረ የምንኖርባትን ዓለም ማለቴ ነው! ስል ሁለቱም እንዲሰሙኝ ጮሁኩኝ። አጯጯሄ ከወትሮው በተለየ በኃይል ስለነበር ከሴት አያቴ ቀድሞ ወንድ አያቴ የሰማኝ ይመስለኛል። ደግሞም ሰምቶኛል ‹የምንኖረው እኔ ቤት አይደል? ሲል ጠየቀኝ።

‹ምነው አብደሃል እንዴ አንተ ልጅ? ቤቱንም ልትሸጠው አስበሃል? አለችኝ ሴት አያቴ አይታኝ በማታውቀው የጥርጣሬ አይን እያየችኝ።

‹የዓለም ፍጻሜ ማለቴ ነው! ስል ዝግ ብዬ ተናገርኩ። ከዓለም እንዳልወጣሁ ትዝ ሲለኝ ‹ስምንተኛው ሺህ ማለቴ ነው› ስል ለማስረዳት ሞከርኩ።

‹ታዲያ እንደዛ በላ ምን ያደናብርሃል! አለችኝ አያቴ የተደናበርኩት እኔ መስያት።

‹ተደናበርኩ እንዴ? ስል ጠየኳት።

‹እናስ! ተደናብረህ ሰው አታደናብር..› ቆጣ አለች።

ይሄ የዘወትር ታሪኬ ነው። ይሄን ነኝ እኔ.. እንዲህ ነው ታሪኬ። ከአምና የተለየ ዛሬ፣ ከትላንት የራቀ አሁን የለኝም። ሁሌም አንድ አይነት ነኝ... እንዲህ እንደአሁኑ። እያደናበርኩና እየተደናበርኩ። አያቴ ውብ ዜማዬ ናት..የጣፈጥኩት.. የጣምኩት.. የላምኩት በእሷ ነው። በአያቴ አለመስማት ውስጥ፣ በአያቴ መጃጃት ውስጥ፣ በአያቴ መደናበር ውስጥ ልክ ያልሆኑ ብዙ ልኮች አሉኝ። ማንም ያለበሰውን የዘመን ጌጥ..የጊዜ ፈርጥ ነፍሴ ገሳ ለብሳለች..።

አያቴ ፈተናዬ ናት..ሳልንገላታባት ሳትንገላታብኝ ቀርታ አታውቅም። አንድ ጊዜ ምን ሆነ መሰላችሁ.. በምታዘክረው የጊዮርጊስ ዝክር ላይ ብዙ ሰው በተሰበሰበበት ያሞገስኳት መስሎኝ ‹ጠላሽ መርዝ ነው! አልኳት። ከዛ ንግግር በኋላ ከአያቴ ጋር አይጥና ድመት ሆንን። ለካ የዶሮ አይን የመሰለ ጠላ ነበር የሚባለው። በዘመነኛ ቋንቋ ያሞገስኳት መስሎኝ አስነወርኳት። ምን ልል እንዳሰብኩ ካስረዳኋት በኋላ ነው እንደ ድሮው የሆነችልኝ።

የሆነው ሆኖ ግን ዜማዬ ናት..በልቤ ብቻ፣ በነፍሴ ብቻ የምዘምራት። በሚኖረኝ እልፍ ነገ ውስጥ ትዝታ ሆናኝ የምትቀመጥ። መርምሬ፣ በርብሬ የማልደርሳት.. አስቤ፣ ተስቤ የማልነካት..የሀሳቤና የምኞቴ የሕልሜም ወደብ።

እያደናገርኳትና እየተደናገረችብኝ ከእሷ ጋር ዝንተዓለም ያንሰኛል..

እያደናገረችኝና እየተደናገርኩባት ከእሷ ጋር ዘላለማት አሁን ናቸው..

# ዓለም አቀፍ



ሩሲያ አሕጉር አቋራጭ ሚሳዔሏን በወታደራዊ ትርዒት ላይ ባቀረበችበት ጊዜ

## ሩሲያ ለመጀመሪያ ጊዜ አሕጉር አቋራጭ ሚሳዔል በዩክሬን ላይ መተኮሷ ተነገረ

**በጋዜጣው ሪፖርተር**

ሩሲያ ዛሬ ከደቡባዊ ከተማዋ አስትራክሃን አሕጉር አቋራጭ ባሊስቲክ ሚሳኤል (አይሲቢኤም) የተባለውን ረጅም ርቀት ሚሳዔል መተኮሷን የዩክሬን አየር ኃይል አስታወቀ።

አየር ኃይሉ እንዳለው በተለያዩ ዓይነት ሚሳዔሎች በተፈፀመው ጥቃት ዲኒፕሮ ክልል ዒላማ ተደርጋለች።

የክልሉ ኃላፊ በተፈፀመው በዚህ ጥቃት የደረሰው ጉዳት በውል ባይታወቅም ቢያንስ 15 ሰዎች ላይ ጉዳት መድረሱን ተናግረዋል። ከተጎዱት መካከል የ16 እና የ17 ዓመት ታዳጊዎች እንደሚገኙበት ጠቅሰው ዘጠኝ ሰዎች በሆስፒታል ሕክምና እየተደረገላቸው እንደሆነ፤ ነገር ግን ስላሉበት ሁኔታ አለመታወቁን የክልሉ ኃላፊ ሴሪይ ሊይሳክ ገልጸዋል።

ቢቢሲ ሩሲያ ዛሬ ጠዋት ላይ በዲኒፕሮ በፈፀመችው የሚሳኤል ጥቃት የደረሰውን ጉዳት የሚያሳዩ ምሥሎች የደረሱት ቢሆንም ጉዳቱን ያደረሰው የትኛው የሚሳዔል ዓይነት እንደሆነ ግልጽ አይደለም።

የዩክሬን ድንገተኛ አገልግሎትም በእሳት የተያያዙ የመኖሪያ ሕንጻዎች እና የወደመ የአካል ጉዳተኞች የማገገሚያ ማዕከልን የሚያሳዩ ምሥሎችን አጋርቷል።

የዩክሬኑ ፕሬዚዳንት ቭላድሚር ዜሌንስኪም ሀገራቸው 'በአዲስ የሩሲያ ሮኬት' መጠቃቷን እና ጥቃቱ የተፈፀመበት መሣሪያ አይሲቢኤም የተባለው የባለስቲክ ሚሳዔል ዓይነት ባሕርይ እንዳለው ገልጸዋል።


ሆኖም ስማቸው ያልተጠቀሰ አንድ የአሜሪካ ባለሥልጣን ወደ ዩክሬን የተተኮሰው ሚሳዔል ባሊስቲክ ሚሳዔል እንጂ አሕጉር አቋራጭ ሚሳዔል አይደለም ማለታቸውን የቢቢሲ የአሜሪካ አጋር የሆነው ሲቢኤስ ኒውስ ዘግቧል።

ሩሲያ በባልስቲክ ሚሳዔል ጥቃት ፈፅማለች ስለመባሏ የተጠየቁት የክሬሚሊን ቃል አቀባይ ዲሚትሪ ፔስኮቭ አስተያየታቸውን ለመስጠት ፈቃደኛ ሳይሆኑ ቀርተዋል። የሀገሪቱ የመከላከያ ሚኒስቴር ባወጣው መግለጫ ላይም ስለጥቃቱ የሰጠው መረጃ የለም።

ሩሲያ ጥቃቱን መፈፀሟ ከተረጋገጠ ሩሲያ በዩክሬን ላይ ወረራ ከፈፀመችበት ጊዜ ጀምሮ በአይሲቢኤም ጥቃት ስትፈፅም ይህ ለመጀመሪያ ጊዜ ይሆናል ሲል ቢቢሲ ዘግቧል።

## አሜሪካ የፀጥታው ምክር ቤት በጋዛ የተኩስ አቁም እንዲደረግ ያቀረበውን የውሳኔ ሀሳብ ውድቅ አደረገች

**በጋዜጣው ሪፖርተር**



አሜሪካና የፀጥታው ምክር ቤት

አሜሪካ የተባበሩት መንግሥታት ድርጅት የፀጥታው ምክር ቤት በጋዛ የተኩስ አቁም እንዲደረግ የቀረበውን የውሳኔ ሀሳብ ድምፅን በድምፅ የመሻር መብትን በመጠቀም ውድቅ አደረገች።

15 አባላት ያሉት ምክር ቤቱ 10 ቋሚ ያልሆኑ አባላት ባቀረቡት የውሳኔ ሃሳብ ለ13 ወራት የዘለቀው ግጭት በአስቸኳይ ያለምንም ቅድመ ሁኔታ ቋሚ የተኩስ ማቆም እንዲደረግ እና ታጋቾቹ እንዲፈቱ በተናጠል ጠይቋል።

በውሳኔው ላይ የተሰጠውን ድምፅ የሻረችው አሜሪካ ምክትል አምባሳደር ሮበርት ዉድ ዋሽንግተን ታጋቾች በአስቸኳይ እንዲፈቱ የሚጠይቅ የውሳኔ ሀሳብ ብቻ እንደምትደግፍ በግልጽ አቋሟን አሳውቃለች ሲሉ ገልጸዋል።

አምባሳደሩ "የጦርነቱ ዘላቂ ፍጻሜ የታጋቾቹን መለቀቅ ማካተት አለበት፤ እነዚህ ሁለት አጣዳፊ ግቦች የማይነጣጠሉ ናቸው ይህ የውሳኔ ሃሳብ ያንን አስፈላጊነት አላካተተም በዚህ ምክንያት አሜሪካ ልትደግፈው አትችልም" ብለዋል።

ዋሽንግተን የተኩስ አቁም ስምምነትን ትፈልጋለች ያሉት አምባሳደሩ ነገር ግን የቀረበው የውሳኔ ሃሳብ ጽሑፍ ለፍልስጤም ታጣቂ ቡድን ሃማስ ወደ ድርድር ጠረጴዛ መመለስ አያስፈልግም የሚል አደገኛ መልዕክት ያስተላለፈ ነበር ነው ያሉት።

የውሳኔ ሀሳቡን ያቀረቡት የምክር ቤቱ ተለዋዋጭ 10 አባላት አልጄሪያ፣ ኢኳዶር፣ ጉያና፣ ጃፓን፣ ማልታ፣ ሞዛምቢክ፣ ደቡብ ኮሪያ፣ ሴራሊዮን፣ ስሎቬኒያ እና ስዊዘርላንድ የውሳኔ ሃሳቡ ውድቅ በመደረጉ በአሜሪካ ላይ ትችት ሰንዝረዋል።

የማልታ የተባበሩት መንግሥታት ድርጅት አምባሳደር ቫኔሳ ከድምፅ ሂደቱ በኋላ ባደረጉት ንግግር “ይህ ምክር ቤት ድምፅን በድምፅ በመሻር መብት ምክንያት በድጋሚ ዓለም አቀፍ ሠላምን እና ደኅንነትን የማስጠበቅ ኃላፊነቱን መወጣት ባለመቻሉ በጣም እናዝናለን” ብለዋል።

የቻይናው አምባሳደር ፉ ኮንግ በበኩላቸው “አሜሪካ እሥራኤልን ለመጠበቅ ድምጿን በሰጠች ቁጥር በጋዛ የሚገደሉት ሰዎች ቁጥር ከጊዜ ወደ ጊዜ እየጨመረ መጥቷል፤ ከማስመሰል እንቅልፍ ከመነሳታቸው በፊት ስንት ሰዎች መሞት አለባቸው?" ሲሉ ጠይቀዋል።

በጥር 20 ከሥልጣን የሚለቁት የአሜሪካው ፕሬዚዳንት ጆ ባይደን ለእሥራኤል ጠንካራ ዲፕሎማሲያዊ እና የጦር መሣሪያ ድጋፍ ማድረጋቸውን ቀጥለዋል በእሥራኤል እና በሃማስ መካከል የተኩስ አቁም ስምምነት ለማድረግ በተለያዩ ጊዜያት ቢሞክሩም አልተሳካላቸውም ሲል አል አይን ዚውስ ዘግቧል።

ማህበራዊ

# ሀገርኛ

# ፍትህ አስከባሪዎቹ ዱቡሻና አፊኒ

ቤዛ እሸቱ

ስሜት ኮርኳሪ ጥቅሶች ከሚነበብባቸው ቦታዎች መካከል የትራንስፖርት አገልግሎት ሰጪ መኪኖች ዋነኞቹ ናቸው። መኪኖች ለአጭርም ሆነ ለረዥም ጉዞ ከተለያየ ቦታ ለሚንቀሳቀሱ ሠዎች ለተወሰነ ሰዓት የጋራ ቤታቸው ይሆናል። ታዲያ በዚህ ቆይታ ዘላቂ ግንኙነት ከመፍጠር አንስቶ የተካረረና ፖሊስ ድረስ የሚደርሱ ጸቦች ይስተናገዳሉ። ለዚህም ይመስላል በተለይ በአዲስ አበባ ታክሲዎች ነገር አትፈልጉን አይነት ጥቅሶችን መመልከት አዲስ ያልሆነው። ከነዚህ ጥቅሶች ውስጥ “ነገረኛ ተሳፋሪ አደባባይ ላይ ወራጅ ይላል” የሚለው ጥቅስ ይገኝበታል። እውነት ነው አንዳንዴ ሕግ ላክብር ያሉ አሽከርካሪና ረዳት ማውረድ የማይቻልበት አደባባይ ላይ ካለወረዳችሁኝ በሚል ትልቅ ጸብ ይነሳል።

እነዚህ ታክሲ ያገናኛቸው ሰዎች ነገ ደግሞ የመገናኘት እድላቸው አነስተኛ ቢሆንም ለያዥ ለገላጋይ የሚቸግር ጸብ ውስጥ ይገባሉ። ከመሃል አንዱ ማለፍን ቢያስቀድም ነገሩ ይበርድ ነበር። ትላንት ማህጸን የተጋሩ የአንድ እናት ልጆች መሃል የተነሱ ሀሳቦች ጸብ ሆነው፤ እናት “ባጠባኋችሁ ጡቶቼ” ብላ እስከትማጸን ሲካረሩ ተመልክተናል። ምርጥ የትዳር ምሳሌ የነበሩ ጥንዶች በቀናት ልዩነት ጸበኛ ሆነው ይገኛሉ። ግጭት በጎረቤት፣ በትዳር አጋሮች፣ በቤተሰብ፣ በጓደኛሞች እንዲሁም በሥራ አጋሮች መሃል ያጋጥማል።

ግጭት በመልካም የሚመኙት ነገር ባይሆንም መፈጠሩ ግን አይቀሬ ነው። ዋናው ቁምነገሩ ግጭቱን በጊዜ መፍታቱ ላይ ነው። በሀገራችን ታዲያ በየአካባቢው እንደየባህሉ “እነሱማ ብለው እንዴት እምቢ ይባላል” ተብለው የሚታወቁ የሀገር ሽማግሌዎችና የሽምግልና ስርዓቶች አሉ። የእርቅ ሥነ-ስርዓት ከሚያካሄዱባቸው ሥርዓቶች መካከል የ‘ዱቡሻ’ና የ‘አፊኒ’ ሥርዓቶች ተጠቃሽ ናቸው። አፊኒ በሲዳማ ብሔር አባላት ሲወርድ ሲዋረድ የመጣ የፍትህ ስርዓትና የእርቅ ሂደት ሲሆን ዱቡሻ ደግሞ በጋሞ አባቶች የሚከናወን የዕርቅና የሰላም ማስከበሪያ ሥርዓት ነው፡፡

በእጃቸው የሚይዙት እርጥብ ሳር መለያቸው የሆነው የጋሞ አባቶች በጋራ የሚመክሩበትና ፍትህ የሚያሰፍኑበት የዱቡሻ ሥርዓት ነው። በዚህ ቦታ በደል ደርሶብኛል፣ ድንበሬ ተገፍቷል፣ ጥቃት ደርሶብኛል፣ሀብቴ ተዘርፏል የሚል አካል የዱቡሻውን መሰብሰቢያ ቀን ጠብቆ አቤት ይላል። ያኔ ተከሳሽ በአጋጣሚ ከዱቡሻው (ባህላዊ ችሎት) ከተገኘ እዛው ይቀርባል። ካልተገኘ ለሌላ ቀን እንዲቀርብ መልእክተኛ ይላክበታል። በቀጠሮው ዱቡሻውን አክብሮ የቀረበን ተከሳሽ መመረቅ የዳኞች የመጀመሪያ ሥርዓት ነው።

በፍርድ ሂደት የተሰየሙ የጋሞ አባቶች የሚይዙት በትርና እርጥብ ሳር መለያቸው ነው። በማኅበረሰቡ ዘንድ እርጥብ ሳር በቁጣ የጋለ ስሜትን በማቀዝቀዝ ወደ ሰላማዊ ስሜት ይቀይራል። በትሩ የእውነተኛውን ስሜት በማወቅ ለእርቅ ያዘጋጃል ተብሎ ይታመናል። በጋሞዎች ዘንድ አባቶች የሚይዙት የበትር ጦር መሬት ላይ ተሰክቶ ሲቆም ማንም ሰው ለእርቅ ይዘጋጃል ተብሎ ሲወርድ ሲዋረድ የመጣ እምነት አለ። በዚህ ሂደት በዳይ የሚክስበት ተበዳይም የሚካስበት ሂደት ይሆናል።

ሆኖም ዱቡሻው ከፍ ያለ አካል ነውና ግጭቶች ሁሉ ወደዱቡሻ አይሄዱም። በጋሞ ባሕል መጀመሪያ ከበዳይም ከተበዳይም ወገን ተወካዮች ባሉበት የዘመድ ጉባኤ ያጋጠሙ ችግሮች ይታያሉ። በዚህ ሂደትም በርካታ ጉዳዮች ይፈታሉ። ሆኖም በዘመድ ጉባኤ በተሰጠው ውሳኔ ካልተስማሙ በአካባቢው የሚገኙና “ጭማ” በመባል የሚታወቁ የሀገር ሽማግሌዎች ጉዳዩን ያዩታል። በዚህ ሂደት ሦስትና ከዛ በላይ በሆኑ የሀገር ሽማግሌዎች ጉዳዩን ይመረምራሉ። ከሀገር ሽማግሌዎቹ እድሜ ከፍ ያለው መሃል ላይ ይቀመጣል። ነገሩን አመዛዝነው የሀገር ሽማግሌዎቹ በዳይን ያርማል ተበዳይንም ይክሳል ያሉትን ውሳኔ ይወስናሉ። ሁለቱም ወገኖች በዚህ ሂደት ከተስማሙ ጸቡ በእርቅ ይጠናቀቃል። ግን እንደዘመናዊው ፍርድ ቤት የይግባኝ መብታቸው የተጠበቀ ነውና በውሳኔው ያልተስማማ አካል ጉዳዩን ወደዱቡሻ የመውሰድ መብት አለው፡፡

በሀገር ሽማግሌዎች ታይቶ ያልተፈታ ችግር ወደዱቡሻ ሥርዓቱ በሚወሰድበት ወቅት የሀገር ሽማግሌዎቹ እስካሁን የመጡበትን ሂደትና የወሰኑትን ውሳኔ ያስረዳሉ። ከዛ በመቀጠል ዱቡሻው ነገሩን ከሥሩ በመመርመር የሀገር ሽማግሌዎቹ ውሳኔ ልክ ከሆነ ያጸኑታል። ውሳኔው ላይ መሻሻል ያለባቸው ጉዳዮች ካሉ በማሻሻል ውሳኔ ያሳልፋሉ። ጉዳዩ በሀገር ሽማግሌዎች ታይቶ በውሳኔው ካልተስማማ ግለሰብ በተጨማሪ ጉዳዩን ወደዱቡሻ በቀጥታ የሚወስዱ አቤቱታ አቅራቢዎችም አሉ።

ተበድያለሁ ሲል ወደዱቡሻው የቀረበው ሰው የመጣበትን ምክንያት እንዲያስረዳ እድል ይሰጠዋል። የሀገር ሽማግሌዎቹ “የሞቱ ሰዎችን፣ ያለን እኛንም እይ፣ ፈጣሪንም ከላይ እይ፣ ዋሽተህ የምትሄድ ከሆነ ቤት አትደርስም፡፡” በማለት እውነት እንዲናገር ያስምሉታል። በማኅበረሰቡ ዘንድ በውሸት ክዶ መሃላ ከፈጸመ በሕይወቱ፣ በንብረቱ፣ በቤተሰቡ ላይ ይደርሳል ተብሎ ስለሚታመን ውሸት በጥብቅ የተከለከለ ነው። የጋሞ አባቶች የተበዳይንም የበዳይንም ሀሳብ በደንብ ያዳምጣሉ። ነገሩን በደንብ አሰላስለውና በጋራ መክረው ሲያበቁ ይበጃል ያሉትን ውሳኔ ያሳልፋሉ፡፡

በአብዛኛው በዱቡሻው የተላለፈ ውሳኔ ሁለቱም ወገኖች የሚቀበሉበት እድል ያመዝናል። አንዳንዴ ከሳሽም የተወሰነልኝ ውሳኔ ያንሳል ሲል፤ እንዲሁም ጥፋተኛ የተባለ አካል ያለጥፋቴ ተፈረደብኝ ሲል ውሳኔውን የማይቀበሉበት ሁኔታ ያጋጥማል። በዚህ ውሳኔያቸው ከጸኑ ከአካባቢው አለፍ ያለውና በርካታ አካባቢዎችን የሚሸፍነው ዱቡሻ ላይ ይግባኝ በማለት የመጨረሻ ውሳኔ ማስወሰን ይችላሉ። በዚህ ሂደትም ውሳኔው ሊጸና ወይም ሊሻሻል ይችላል። ሆኖም አብዛኛው ጉዳዮች ይግባኝ ጋር አይደርሱም።

በመጀመሪያው ዱቡሻ የአካባቢው ሽማግሌዎች ተከሳሹን ከዱብሻው ገለል አድርገው በመውሰድ ጥፋቱን ክዶ ከሆነ ጦሱ ለሱ ብቻ ሳይሆን በንብረቱም እንዲሁም በቤተሰቡ ጭምር እንደሚደርስና እውነቱን ቢናገር እንደሚሻል ያግባቡታል። ያኔ የካደው መልሶ ጥፋቱን ያምናል። ይህ ሳይሆን ቢቀር ነገሩን እንዲያስበው የማሰቢያ ቀን ይሰጠዋል። ያኔ ቤተሰቡና የአካባቢው ሰዎች ጉዳዩን ዘርዝረው በማስረዳት “እንዴት አልታየህም በዚህ ምክንያት እኮ ጥፋተኛ በመሆንህ ውሳኔው ተገቢ ነው” ይሉታል። በማግስቱ ወደዱቡሻው በመመለስ ጥፋቱን ማመኑንና የተወሰነበትን ካሳ ለመክፈል መስማማቱን ያሳያል። በጋሞዎች ይቅርታ ትልቅ ቦታ አለው። የተፈጠረ ጸብ በእርቅ ከተደመደመ በኋላ የታረቁ ወገኖች እስከጋብቻ በሚደርስ ዝምድና ድረስ ግንኙነታቸው ወደ ቀድሞው ቦታው ይመለሳል። ጋሞዎች በሙሉ መተማመን ዱቡሻ ላይ ቀርቦ የማይፈታ ችግር የለም ይላሉ።

ከዱቡሻ ጋር የተወሰኑ የጋራ እሴቶችን የሚጋራውና የሲዳማዎች ችግርና ግጭት መፍቻ ባሕላዊ የፍትህ ስርዓት “አፊኒ” ይሰኛል። “አፊኒ” ሰማችሁ? አወቃችሁ? አያችሁ ወይ? ማለት ነው። ሲዳማዎች አላግባብ የዘመዳቸው ደም በከንቱ ቢፈስ እሬሳውን እቤት አስቀምጠው ሰማችሁ ወይ ሲሉ “አፊኒ” ይላሉ። ማኅበረሰቡ እነሱ ላይ የደረሰው መጥፎ ነገር ሰምቶ ከበዳያቸው ጋር ተባብሮ ፍትህን አይነፍጋቸውምና ፍትህ እንደሚያገኙ በመተማመን “አፊኒ” ሲሉ ጆሮ ይሻሉ። በሲዳማ ባሕል ተበዳይ “አፊኒ” ብሎ በአቅራቢያው ላገኛቸው ሰዎች ችግሩን ካስረዳ በኋላ ነገሩ በረድ ይላል። በባሕሉ ማንኛውም ተበዳይ ቀጣይ እርምጃ ከመውሰዱ በፊት “አፊኒ” በማለት የደረሰበትን ችግር የማሳወቅ ግዴታ አለበት።

“አፊኒ” ሲባል ነገሩ ከመክረር ይልቅ ለውይይት ክፍት ይሆናል። ተናዶ የመጣ አካል “አፊኒ” ሲባል ከንዴቱ በተወሰነ ደረጃ ሰከን የማለት እድል ያገኛል። በአፊኒ የሚዳኘው የከረረ ግጭት ብቻ አይደለም። አባቴ ትክክል አይደለም በድሎኛል ያለ ልጅ ለአባቱ እኩያ አፊኒ ሲል ነገሩን ያስረዳል። በአባቴ ተበድያለሁ የሚልን ሕጻን ሀሳብ ሳይንቁ የሚሰሙት አባቶች ለመፍትሄ አባትን ያናግራሉ። በተመሳሳይ ልጄ አጥፍቷልና ቅጣት ያሻዋል ያለ አባት ልጁ ላይ እጁን ከመሰንዘሩ በፊት አፊኒን ያስቀድማል። በባሕሉ ሳያስበው ቡጢ የተሰነዘረበት ሰው ቢኖር እንኳን ቡጢውን መመለስ ቢፈልግ መጀመሪያ “አፊኒ” ማለት አለበት። ይህ ሳይሆን ቢቀርና የተሰነዘረበትን ቡጢ ልመልስ ብሎ ቢሰነዝር ጥፋቱ ከመጀመሪያው ተማቺ ይልቅ በሁለተኛው ላይ ያይላል። ስለዚህም አፊኒ አላልክም በሚል ተመቺው ከተቀጣ በኋላ የመጀመሪያው ተመቺ “ለምን መታሃው?” ተብሎ ይጠየቃል። ግጭትን ማስቀረት ባይቻልም አፊኒ የምትለዋ ቃል ሰዎች ከገቡበት ግጭት የምታቀዘቅዝና ነገሩን በብልሃት የሚያመዛዝኑበት አቅም ይሰጣቸዋል፡፡

በሲዳማ አፊኒ ከቤት እስከ አደባባይ ጥቅም ላይ ይውላል። የሚጣሉ ሁለት አካላትን ያየ አካል “እኔ ገለልተኛ (ሦስተኛ አካል) ነኝና እናንተን ላስማማ አካል ወደማጉደል ሕይወት ወደማጥፋት አትሂዱ፡፡” በማለት ጊዜ ወስዶ የእነሱን ጉዳይ ለማየት ግብዣ ያቀርባል። ከተቻለ በአቅራቢያ በሚገኙ ሰዎች ተዳኝተው ጉዳዩ ይበርዳል። አለፍ ካለ ክሶች የሚታዩበት ባሕላዊ ፍርድ ቤት አለ። እዚህ ፍርድ ቤት የሚታደሙት በሀገሬው ይሁንታን ያገኙ ሽማግሌዎች፣ ተበደልን ሲሉ አፊኒ ባዮች፣ አጥፍተዋል የተባሉ እንዲሁም የፍርድ ሂደቱን መከታተል የፈለገ ማንኛውም አካል መከታተል ይችላል። ፍትህ ፈልጎ “አፊኒ” ያለ በደሌን ሰማችሁ ወይ? ሲል ወደ ፍርድ ሸንጎ የመጣ አካል በደሉን የማስረዳት ቅድሚያ እድል ይሰጠዋል። በዚህም የደረሰበትን በደል አንድ በአንድ ዘርዝሮ ያቀርባል። በቃል የቀረበውን አቤቱታ ሰምተው ሲጨርሱ ክስ የቀረበበት በአካል ቀርቦ መልስ ይሰጥ ዘንድ መልእክተኛ ይልኩበታል፡፡

በአፊኒ ስርዓት ተጠሪ የተጠራበትን ቀንና ሰዓት አክብሮ መገኘት የግድ ነው። አፊኒን አክብሮ በሸንጎው ላይ ያልተገኘ ለአምላክ ይነገርበታል የሚል እሳቤ አለ። ስለዚህ ሁሉም ቅሬታ የሚቀርብበት አካል ይሄን ስለሚፈራ የተባለውን ቀጠሮ አክብሮ ይገኛል። ከሳሽም ተከሳሽም ጉዳዩን ያስረዳሉ። የሀገር ሽማግሌዎቹ የሰሙትን ሲያሰላስሉ ቆይተው እውነታው ላይ ደርሰናል ብለው ሲያስቡ እንደሀገሩ ደንብ ሀሳባቸውን ከማሳወቃቸው በፊት “አፊኒ” ይላሉ። ይህ አፊኒ ትርጉሙ ሰማችሁን ወይ? ማለት ሲሆን ሌላኛው እውነታው አንተም ይመለከትሀል ሀሳቡ ለመስጠት ተዘጋጅ ማለትም ነው። በአፊኒ እውነታው የአንድ አካል ብቻ ሳይሆን ሁሉም የታየውን ሀሳብ እየሰነዘረ የጋራ እውነት ላይ ይደረሳል። በሸንጎው ላይ የተገኘ በሙሉ ፍትህ ለማስፈን የሚጠቅም ሀሳብ ያገኘ ሲመስለው አፊኒን እያስቀደመ ይናገራል፡፡

በአፊኒ ሂደት መካድም ሆነ መዋሸት ፍጹም አይታሰብም፡፤ በዘመናዊ የፍትህ ስርዓት ታይቶ በምስክር ወይም በማስረጃ እጦት የቀረ ሂደት ወደ አፊኒ መጥቶ የመታወቅ እድሉ ከፍ ያለ ነው። በሀገሬው ደንብ በአፊኒ የካደ በሕይወት አይቆይም የሚል እምነት አለ። ስለዚህ ሌላ ቦታ የካደ ሁሉ አፊኒ ላይ ያምናል። በየክፍሉ ሲከናወኑ የነበሩ የፍርድ ሂደቶች ከተጠናቀቁ በኋላ ሁሉም በጋራ ተሰብስበው የጎሳ መሪ (ጋና) ባሉበት ፍርዳቸውን ያቀርባሉ፡፡አልተስማማሁም የሚል ተቀጪ ወይም ተካሽ ካለ መሪው መርምረው ውሳኔው ልክ ነው ካሉ ያጸኑታል። ልክ አይደለም ካሉ ጉዳዩ በድጋሚ ይታያል። ጋናው ነገሩን መርምረው የሚሰጡት ውሳኔ የመጨረሻው ነው።

በአፊኒም ሆነ በዱቡሻ በዳዮች ይቅርታ የመጠየቅና የመካስ ግዴታ ተጥሎባቸዋል። በተመሳሳይ ተበዳይ ወገኖችን የይቅርታ ልብ እንዲኖራቸው ባህሉ ኮትኩቶ አሳድጓቸዋል። ሁለቱም ወገኖች የይግባኝ መብታቸውን በመጠቀም እስከመጨረሻው ደረጃ የመሄድ መብት አላቸው። ሆኖም በሕብረተሰቡ ስምምነት የመጨረሻ ውሳኔ ሰጭ አካልን ውሳኔ መቀበል አማራጭ የሌለው ግዴታ ነው፡፡

በከተማ አካባቢ የሚፈጠሩ ግጭቶች የመልካሙ ተበጀ “አይረሳም ተበዳይ ለካ የበደልሽኝን እንዳልረሳ ሆኛለሁ ...” የሚለውን ዘፈን በማቀንቀንና ለይቶለት ለቂም በቀል ባይነሳም የበዳይን ውድቀት ለማየት በመመኘት ነው። በዱቡሻና አፊኒ ግን በዳይ ጥፋቱን አምኖ ይቅርታ መጠየቅና መካስ ተበዳይም ይቅርታን መቀበል ግዴታ ነው። ሆኖም ውሳኔውን አልቀበልም የሚል አካል ካለ ማኅበረሰቡ ያገለዋል። ሠርጉ አይደምቅ፣ ሐዘኑ የጋራ አይሆንም። ሁሉም ይሄን ስለሚያውቅና የወጣበት ማኅበረሰብ የማይቀየር ሕግ ነውና የእርቅ ውሳኔውን ያከብራሉ።



የዱቡሻ ሥርዓት ሲካሄድ



የአፊኒ ሥርዓት ሲካሄድ

ይህ አምድ በተለያዩ ፖለቲካዊ ኢኮኖሚያዊና ማህበራዊ ጉዳዮች ዙሪያ ዜጎች ነፃ ሀሳባቸውን የሚሰጡበት ነው:: በዓምዱ ላይ የሚወጡ ጽሁፎች የዝግጅት ክፍሉን አቋም አያመለክቱም::

ፖለቲካ እና ወቅታዊ

ነፃ ሃሳብ

# ያቃተን ወደሚበልጠው መመልከት ነው

**ቴልጌልቴልፌልሶር (የኩሽ አሽክታብ)**

ከምንምነት ለመውጣት ሀገር ያስፈልገናል። የነበሩንን ለማስቀጠል፣ ለሚኖሩን ዋጋ ለመስጠት የትቅቅፍና የትስስብ ፖለቲካ ያስፈልጋል። የኃይል ርምጃ የሚያሳጣው ሀገር ነው ። በዓለም ላይ ታሪክ እንዳይረሳቸው ሆነው የተመዘገቡ መጥፎ ታሪኮች በእልህ፣ በቁጣ፣ በጥላቻ፣ በዘረኝነት የተከሰቱ ናቸው። አንድ ነገር ከመከሰቱ በፊት መጠንቀቅ እንጂ ከተከሰተ በኋላ ወደነበረበት ለመመለስ አስቸጋሪ ነው::

‹ቤት በጥበብ ይሰራል በማስተዋልም ይጸናል› የሚል ቅዱስ ቃል በቅዱስ መጽሀፍ ላይ አውቃለው። በእውነትም ቤት ለመስራት፣ ጎጆ ለመቀለስና ትዳር ለማቆም የበረታ እውነትነት አለው። በዚህ ሀሳብ ውስጥ ቤት የሚለውን ቃል እንደሀገር፣ እንደሕዝብ፣ እንትውልድ ልንተረጉመው እንችላለን። ኢትዮጵያን እንደቤት ብንወስዳት ጥበብና ማስተዋል የታከለበት አብሮነታችን፣ ትስስራችን፣ ወግ ባህላችን፣ ታሪክ እሴቶቻችን ደግሞ የሕልውናችን ማሰሪያ ሆነው የሚነሱ ናቸው::

በሰላም ለሰላም እና በጦርነት ለሰላም የተለያዩ እሳቤዎች ናቸው። በነዚህ ሁለት የተለያዩ ምርጫዎች ዓለም ጥንድ ጎራዎችን ፈጥራለች። እንደእኛ ሀገር የፖለቲካና የኃይል ልምምድ ብንነሳ ሁለተኛው እሳቤ ላይ እናርፋለን። ሰላምን በኃይል ለመውለድ የምናደርገው የእልህ ትንቅንቅ ስልሳ ዓመታትን ተሻግሮ ዛሬም አልበረደም። እንደ እውነቱ ከሆነ ይሄ አካሄዳችን ትርፋችንን ከማጉደልና ኋላ ቀርነታችንን ከማጉላት ባለፈ የሰጠን የክብር ስም የለም::

በስልሳ ዓመታት የፖለቲካ ትርክት ውስጥ እንደሀገር ብዙ ጎሎብናል። ዛሬ ላይ ለእርስ በርስ ጥላቻ መንገድ የከፈቱ የዘረኝነትና መሰል አክሳሪ የጥፋት ምንጮች በዛ ማህጸን የተጸነሱ ስለመሆናቸው መስካሪው ብዙ ነው። ስልሳ ዓመታትን በጦርነትና በመሰል የፖለቲካ ትንቅንቅ መባደን ለድሀ ሀገርና ሕዝብ ምን ማለት እንደሆነ ግልጽ ነው። ያን ከመሰለው የእርስበርስ ትንቅንቅ ወጥተን ስለሀገር መመካከሩ የበለጠ ዋጋ እንዳለው በመረዳት የሚከብድ አይደለም::

በጦርነት አቅሟን ላጣችው ሀገራችን ሰላም እና የሰላም ጉባኤ ምን ማለት እንደሆነ ለሁላችንም ግልጽ ነው። ላሳለፍነውና ለምናሳልፈው ብዙሀን መሻት እጅግ ዋጋ ካላቸው ቁምነገሮች መሀል የመጀመሪያው የሰላምን ዋጋ የተረዳ ፖለቲከኛ መፍጠር ነው። ፖለቲካው በሰላማዊ ሀሳብ ከዳበረ በኃይል የሚፈታ ግለሰባዊና ማኅበረሰባዊ ችግር አይኖርም። እንደሀገር የሚነሱ ማናቸውም ጥያቄዎች በሕገመንግስቱ እንዲፈቱ አስገዳጅ ስርዐት ይሰጣል።

በብዙ ነገር ላይ ፈር ስተናል። ፖለቲካው ፈር ስቷል፣ ፖለቲከኛው ፈር ስቷል። የዚህ ድምር ውጤት ደግሞ ጦርነት ሆኖ በተለያየ ዘመን ላይ አስተውለናል። ደፋቸውም በመከራና ስቃይ፣ ሞትና ጉስቁልና ሆኖ ተመልክተናል። የዚህ ሁሉ ሰለባ ደግሞ ሕዝብ ነው። የሕዝብ እዬዬ ከፖለቲከኞች አሸሽ ገዳሜ እንደሚወጣ የታወቀ ነው። የሀገር ዋይ ዋይ እንደዚሁ ፈር በሳቱ ሀሳብ የለሽ ስሜታዊነት በኩል የሚታዩ የድርጊት ውጤቶች ናቸው።

ቅደም ተከተሉን የጠበቀ ፖለቲካ መፍጠር ከሰነበቱብን የጦርነት እና መሰል ልምምዶች ለመራቅ እንደ መፍትሄ የሚወሰድ ቀዳሚ አማራጭ ነው። በብዙ ችግር ውስጥ ተዘፍቀን የምንገኘው ቅደም ተከተሉን ባልጠበቀ አካሄድ ነው። በጦርነትና በመሰል የእርስ በርስ ፍትጊያ ስልሳ ዓመታት የዘላለምን ያክል ነው። በተለይ ደግሞ እንደእኛ ላሉ ራሳቸውን በምግብ ላልቻሉ፣ በውጪ ሀገራት ርዳታ ለሚኖሩ ትርጉሙ ከዚህም በላይ ነው::

> **ነውር ወለድ የትርክት እዳችን እንደበጎ ውርስ ከትውልድ ትውልድ ተላልፎ የመጣንበትን አዘንግቶ የምንሄድበትን እንዳያሳጣን ቆም ብለን ልናስብ ይገባል:: ትውልድ ሀገር ይፈልጋል፣ ራዕይ ሀገር ይፈልጋል፣ ታሪክ፣ እሴት፣ ባሕል ወግ በሀገር በኩል የተዋቡ ናቸው:: ክብር ሀገር ይፈልጋል፣ ማንነትና ሉአላዊነት በሀገር የነቁ ናቸው:: ሀገር የሌለው ለእኚህ ሁሉ ባዕድ ነው:: እነዚህ ሁሉ የሌሉት ደግሞ ምንም ነው**

ቅደም ተከተላችን ከሰላም ወደሰላም ነው። ከጦርነት ወደሰላም የነበረውን ፖለቲካዊ መርህ ሽረን ከሰላም ወደሰላም ሽግግር ያስፈልገናል። ሀገር ሰላምን እና ሕዝባዊነትን ባስቀደመ ፖለቲካዊ፣ ኢኮኖሚያዊና ማኅበራዊ ቅደም ተከተል ውስጥ ካልሆነች በጦርነትና በመሰል የጥላቻ ትርክቶች ዋጋ ለመክፈል ቅርብ ናት። የውሀውን ምንጭ አድርቆ ውሀ ፍለጋ የሚሄድና የውሀውን ምንጭ ጠብቆ በውሀ የሚረካን ሁለት ግለሰቦች እንዴት ትገልጽዋቸዋላችሁ? ምንጩን ያደረቀው የመጀመሪያው ግለሰብ በተፋለሰ ቅደም ተከተል ውስጥ ነው ይሄ ያሳለፍነውን ስድስት አስርት ዓመታት የፖለቲካ ጉዞ ሲያመላክት ምንጩን ጠብቆ በውሀ የረካው ግለሰብ ደግሞ በተዋበ ቅደም ተከተል ውስጥ ያለ የምንመኘውን ነገ የሚወክል ነው::

የሰላም ምንጮች ያስፈልጉናል። ምንጮቻችን ባህሎቻችን እና እሴቶቻችን ናቸው። ምንጮቻችን የመከባበርና የመቻቻል ጥንተ ወጎቻችን ናቸው። ምንጮቻችን በጋራ ተቀድተው በጋራ የሚፈሱ የትስስር ልማዶቻችን ናቸው። እነዚህን አፍርሰን የምንገነባው ሀገር የለም። እነዚህን ንደን የምንማግረው ትውልድ የለም። እንደሀገር ለመፍጠር እንደግለሰብ መበርታት አለብን። እንደማኅበረሰብ ለመበርታት እንደፖለቲካ መዘመን አለብን። እንዲህ ያለው አካሄድ ነው በጸና ቅደም ተከተል ውስጥ አኑሮ የሰላም ጀምበር የሚፈነጥቅልን::

ዝማኔ የሀሳብ ሙላት ነው። በሀሳቡ ያልዘመነ ጭንቅላት በምንም ቢበረታ ዋጋ አያወጣም። በፖለቲካውም ሆነ በሌሎች ዘርፎች ላይ ልቀው በመታየት ፊተኛ የሆኑት ሀሳባውያን ናቸው። ሀሳባውያን ጦርነትን ከነመንስኤው ቆፍረው የቀበሩ ናቸው። ማንም ሰው በየትኛውም ልዩነቱ ላይ በመነጋገር መግባባት ይችላል ባይግባባ እንኳን በልዩነት ውስጥ ወደሚበልጠው ማስተዋል ይችላል በሚል ምልከታቸው ይታወቃሉ። ወደሚበልጠው ካስተዋልን በትናንሽ ነገሮች ጦር መሳበቃችን ይቀራል::

ሀገር፣ ሕዝብ፣ ትውልድ ለየትኛውም ፖለቲከኛ ፊተኛ ጉዳዮቹ ናቸው። ታሪክ፣ ባሕል፣ እሴት በየትኛውም የፖለቲካ ሜዳ ላይ የአንድነት ቀለሞች ናቸው። እነዚህን መመልከት ሲያቅተን በሞራልና በሀሳብ ዝለን እንደጦርነት ላሉ ትናንሽ ነገሮች እንረታለን። በትናንሽ ነገር መረታት ደግሞ ዋጋ ያለውን ውድ እውነት በማሳጣት ዋጋ ለሌለው ርካሽ ሀሰት ይዳርጋል። በእውነቱ ያቃተን ወደሚበልጠው መመልከት ነው። የሚበልጠው ደግሞ በሚበልጥ ሀሳብ የሚደረስ እንጂ በኃይል የሚደርስ አይደለም።

ሀሳብ ሀገር የምትድንበት፣ ትውልድ የሚሸርበት የመፍትሄና የበጎ እይታ መገኛ ነው። በዓለም ላይ ጦርነትን ከሚሽሩ አዋጪ የሰላም መንገዶች መሀል ዋነኛው የመነጋገር ባህል ነው። የመነጋገር ባህል ደግሞ ከታች ጀምሮ ወደላይኛው የስልጣን ከፍታ እያደገ የሚመጣ ከሁሉ ለሁሉ የሆነ ነጻ አውጪ የድል ፍኖት ሊባል ይችላል። ይሄን የድል መንገድ ብዙ ሀገራትን ከመከራ የታደገ ለእኛም የጦርነት ትንቅንቅ መፍትሄ የሚሰጥ ነው::

ድል ያለው ሰላም ውስጥ ነው። ሌላው የድል መንገድ ሁሉ አክሳሪ እና አውዳሚ ነው። በተለይ ሰላምን በጦርነት ለማምጣት መሞከር የተሳሳቱ ከሚባሉ የሰላም አካሄዶች ሁሉ የባሰው እና የከፋው ነው። በዚህ እውነታ በኩል ብንመለከታቸው የስልሳ ዓመት የጦርነት ታሪኮቻችን ምን ያክል ዋጋ እንዳስከፈሉንና እንዳሳጡን ለመረዳት አይከብድም። የነጻነት መዳረሻቸውን በሰላም በኩል ያደረጉ ከሌላው በተሻለ አሸናፊዎች ናቸው። እኚህ ልምምዶች እኛም ሀገር ተለምደው የጦርነት የአቅጣጫዎቻችንን ቢቀይሩልን መልካም ነው::

ስለሰላም የሚያወጋ የምክክር መድረክ ለእርቅና ለአንድነታችን ወሳኝ ነው። ሀገራዊ ምክክርን የመሰሉ ስለሰላም በሰላም የቆሙ፣ አስታራቂና አግባቢ የአንድ ዓላማ ጉባኤዎች ወሳኝነታቸው እሙን ነው። አንድ ዓላማን ያነገቡ የወንድማማቾች የሰላም ሕብረት እንደሚያስፈልገን ሀቅ አለው። እነዚህ ሰላም ተኮር የእርቅና የተግባቦት ልምምዶች እንደመጣንበት ስልሳ ዘመን የጦርነት ታሪክ ሁሉ ስለሰላም ልማድ በመሆን ነጋችንን የሚወስኑልን ናቸው::

ለአንድ ዓላማ በአንድነት መቆምን የመሰለ የሉአላዊነት ተገን የለም። በጦርነት የወየቡ የታሪክ እና የክብር መልኮቻችን ወደቀድሞ ይዞታቸው ተመልሰው በኢትዮጵያዊነት የሚሞሸሩት ስለሰላም ስናብር ነው። በጦርነት ምን እንዳጣንና ምን እየጎደለብን እንዳለ ማወቅ አለብን። በዚህ ስልጡን ዘመን ላይ በሀሳብ ማሸነፍ ካልቻልን ሌላ የማሸነፊያ አማራጭ አይኖረንም ቢኖረን እንኳን እንደጦርነት ከብዙ ዋጋ መክፈል በኋላ ባለ መጨባበጥ በኩል ነው::

የአንድ ነገር ዋጋው ምን ያክል እንደሆነ ለማወቅ በግለሰብ ሳይሆን በሕዝብና ሀገር መሰላት አለበት። ጦርነት ከፋች የሆኑ ምክንያቶቻችን በግለሰብ የተሰሉ ሀገርና ሕዝብን ያላካተቱ ናቸው። ሀገርና ሕዝብ ያልተሰላበት የትኛውም ነገር ዋጋ አስከፋይ ነው። ከአንድና ሁለት ወገን ወጥተን ወደሰፊውና ወደብዙሀኑ እንመልከት። ሀገር እያሳጣ፣ ትውልድ እያቀነጨረ ባለነገር ውስጥ ዋጋ የለም።

"ከድጡ ወደማጡ " የሚለው አባባል ከባሰ ወደባሰን ለመግለጽ የተሰጠ አባባል ነው። መጥፎ ታሪኮቻችን ካላስተማሩን፣ ከትላንት ጠፉቶቻችን ካላሰላሰልን ከባሰ ወደባሰ ጉዞ ላይ እንደሆንን አመላካች ነው። ጦርነት ተደጋግሞ አይደለም ለአንድ ጊዜ ቢሆን እንኳን ዋጋ አስከፋይ ነው። የእኛ የጦርነት ታሪክ ደግሞ የረጅም ጊዜ ታሪክ ነው። ከድጥ መውጣት አልቻልንም። ነጋ ጠባ ወደባሰ ንትርክ እያቀናን ነው::


ሰላምን በኃይል የማምጣት የቆየ ልምምዳችን ተቀይሮ ኢትዮጵያን እንደ አዲስ መፍጠር አለብን። ያለን ትንሽ ነገር ነው እሱኑ ለጦርነትና ለእርስ በርስ ግፊያ ሰጥተን እጣ ፈንታችን ምን ሊሆን ነው? አይደለም ለድሀ ሀገርና ሕዝብ ቀርቶ ላላቸውም ቢሆን ጦርነትና ሰላም አብረው የሚቆሙ አይደሉም። በሰላም ለሰላም አብሮ መቆምን፣ ኢትዮጵያ መባልን፣ በወንድማማች መጠራትን ልንለማመድ ግድ ይለናል።

ፖለቲካ ወለድ የሆኑ ቅየቶች ቢያጨቀዩትም ሰላም የሁሉም ፍጥረቶች የመኖር ዋስትና ሆኖ በተፈጥሮ የተሰጠ ስጦታ ነው። አንዳንድ ነገሮች ከእጅ እንዳይወጡ አጥብቆ መያዝ እንጂ ከወጡ በኋላ ለመመለስ ብዙ ዋጋ ነው የሚጠይቁት። ሀገር ተረት ተረት የላትም። በተረት ሁሉም ተረት ማብቂያ አለው። ሁሉም አፈታሪክ ተረት ተረት ብሎ ጀምሮ አፌን በዳቦ አብሱ ብሎ የሚያበቃ ነው::

የእኛ የጦርነት መከራ የት ጋ..መቼ ይሆን ማብቂያው? ለሁልጊዜ ጦርነት ይቻላል? ለሁልጊዜ ገሎ መሞት ይሆናል? ከማጥ የሚያወጡ፣ ከድጥ የሚታደጉ የሰላም መንፈሶች ለዚህ ትውልድ እና ለዚህ ፖለቲካ ዋጋቸው ከፍ ያለ ነው። ሀገር የሚሰጡ፣ ትውልድ የሚያቆዩ የትርክት ውርሶች ያስፈልጉናል።

ነውር ወለድ የትርክት እዳችን እንደበጎ ውርስ ከትውልድ ትውልድ ተላልፎ የመጣንበትን አዘንግቶ የምንሄድበትን እንዳያሳጣን ቆም ብለን ልናስብ ይገባል። ትውልድ ሀገር ይፈልጋል፣ ራዕይ ሀገር ይፈልጋል፣ ታሪክ፣ እሴት፣ ባሕል ወግ በሀገር በኩል የተዋቡ ናቸው። ክብር ሀገር ይፈልጋል፣ ማንነትና ሉአላዊነት በሀገር የነቁ ናቸው። ሀገር የሌለው ለእኚህ ሁሉ ባዕድ ነው። እነዚህ ሁሉ የሌሉት ደግሞ ምንም ነው። አበቃሁ::

# ስፖርት



# ኮንጎን በሜዳዋ ካሸነፍን ሌላውን የማናሸንፍበት ምክንያት የለም

*-አሠልጣኝ መሳይ ተፈሪ*

**ቦጋለ አበበ**

የኢትዮጵያ ብሔራዊ ቡድን(ዋልያዎቹ) ለ2025 የሞሮኮ አፍሪካ ዋንጫ ለመሳተፍ ከምድብ ማጣሪያ መውደቁን ቀደም ብሎ ማረጋገጡ ይታወቃል። ዋልያዎቹ በምድብ ስድስት ከዲሞክራቲክ ኮንጎ፣ ጊኒና ታንዛኒያ ጋር ተደልድለው ባደረጓቸው ስድስት የማጣሪያ ጨዋታዎች በአራቱ ተሸንፈው አንዱን በማሸነፍ አንዱን ደግሞ አቻ በመለያየት ወደ አፍሪካ ዋንጫው የሚያደርጉት ጉዞ ተቋጭቷል።

ይህንንም ተከትሎ በመጨረሻዎቹ ሁለት የማጣሪያ ጨዋታዎች ጊዜያዊ ዋና አሠልጣኝ ሆነው ቡድኑን የመሩት አሠልጣኝ መሳይ ተፈሪ ትናንት ጋዜጣዊ መግለጫ ሰጥተዋል። ዋልያዎቹን ከአሠልጣኝ ገብረመድኅን ኃይሌ ተረክበው ካደረጋቸው ሁለት ጨዋታዎች አንዱ አሸንፈው በአንዱ የተሸነፉት አሠልጣኝ መሳይ ተፈሪ፣ በምድብ ማጣሪያው ቀዳሚ ሆና ያለፈችው ኮንጎን በሜዳዋ 2ለ1 አሸንፈው በታንዛኒያ ደግሞ 2ለ0 ተሸንፈዋል።

በመጨረሻው የማጣሪያ ጨዋታ ባለፈው ማክሰኞ ምሽት ጠንካራዋን ኮንጎ ቀደም ብላ ወደ አፍሪካ ዋንጫ ማለፏን ብታረጋግጥም ዋልያዎቹ ማሸነፋቸው ያልተጠበቀ ነበር። አሠልጣኝ መሳይ ይህንን ድል በተመለከተ ‹‹ይህ ድል ለእኔም ለተጫዋቾቹም ትርጉም አለውና ማስቀጠል



ጊዜያዊ ዋና አሠልጣኝ መሳይ ተፈሪ ዋልያዎቹን ለቻን ውድድር ለማሳለፍ እንደሚሠሩ ገልፀዋል፣

አለብን፣ ኮንጎን ሜዳው ላይ አሸንፈን ከወጣን ሌላውን የማናሸንፍበት ምክንያት የለም፣ ፈተናው ቀላል አይደለም፣ ያም ሆኖ ነገ ከነገ ወዲያ ከሌላው ጋር ተፎካካሪና አሸናፊ የምንሆንበትን ነገር መፍጠር እንችላለን።›› በማለት ተናግረዋል።

አሠልጣኙ ኮንጎን ስላሸነፉበት ጨዋታ ሲያብራሩ፣ ‹‹ለተጋጣሚዎቻችን ተገቢ ያልሆነ የተጋነነ ግምት እንደምንሰጥ እረዳለሁ። ፕሮፌሽናል ናቸው፣ ከእኛ በአካል ብቃትም ይበልጣሉ ወዘተ የሚሉ ተገቢ ያልሆኑ በራስ መተማመን እንዳይኖረን የሚያደርጉ አስተሳሰቦች አሉ። ይህን ለማስቀረትና እኛ እነሱን የምንበልጥባቸው ነገሮች እንዳሉ ለማሳየት ተሞክሯል። ማሸነፍ የምንችልባቸው ነገሮች ላይ ተነጋግረናል። ግቦች ከተቆጠሩብን በኋላ ሳይሆን በሙሉ የጨዋታ ጊዜ ማጥቃትና ማሸነፍ እንችላለን ብለን ወደ ሜዳ ገብተናል›› ብለዋል።

የዋልያዎቹ ከጨዋታ አስቀድሞ አላስፈላጊና ልክ ያልሆነ ፍርሃት ሊቀር እንደሚገባ የገለፁት አሠልጣኝ መሳይ፣ በቴክኒክ፣ ታክቲክና አካል ብቃት ላይ በደንብ መዘጋጀት እንዲሁም ስለራሳችንና ተጋጣሚያችን ጠንቅቀን ማወቅ የሚፈጥረው የሥነ-ልቦና ጥንካሬ እንዳለ ባስረዱበት መግለጫ፣ ቡድናቸው ኮንጎን ለማሸነፍ በተጫዋቾቻቸው ላይ የነበረው ተነሳሽነት ትልቅ እንደነበረ አስታውሰዋል።

የመጨረሻዎቹን ሁለት ጨዋታዎች በድል ለመወጣት ተጫዋቾች የቻሉትን እንዳደረጉ ገልፀው፣ በታንዛኒያው ጨዋታ ድል ባይቀናቸውም ኮንጎን በተለይም ከረጅም ጊዜ በኋላ ማሸነፉ ትልቅ ትርጉም እንዳለው አብራርተዋል። ‹‹ወደ አፍሪካ ዋንጫ እንደማናልፍ ቀደም ብለን ብናረጋግጥም የክብር ጉዳይ ነው፣ የወዳጅነት ጨዋታም ቢሆን በደረጃችን ላይ የሚፈጥረው ልዩነት አለ›› ሲሉም ገልፀዋል።

አሠልጣኝ መሳይ ተፈሪ በጊዜያዊ ዋና አሠልጣኝነት ዋልያዎቹን በመምራት በሀገር ውስጥ ሊጎች ብቻ የሚጫወቱ ተጫዋቾች የሚሳተፉበት የአፍሪካ ዋንጫ(ቻን) ማጣሪያ ጨዋታዎችን ያደርጋሉ። በዚህ ማጣሪያ ወደ አፍሪካ ዋንጫ ካለፈችው ከሱዳን ጋርም ይገናኛሉ። ለዚህ ጨዋታም ለዋልያዎቹ በተለይ የአካል ብቃት፣ ሥነ-ልቦና እና ቪዲዮ ትንተና ባለሙያዎች አስፈላጊ መሆናቸውን ጠቁመዋል።

እንደ አሠልጣኙ ገለፃ፣ በአፍሪካ ዋንጫው ማጣሪያ ጨዋታ የመረጣቸው ተጫዋቾች ቻንን ታሳቢ ባደረገ መልኩ ነው። ወጣት ተጫዋቾች ቡድኑን ተቀላቅለዋል፣ እነዚህን ልምድ ካላቸው ጋር በማጣመር ለቻን ውድድር ለማለፍም ይጫወታሉ። ለዚህም ‹‹አሁን ያለውን ሞራል ከሚመለከተው ጋር ተባብረን ማስቀጠል አለብን። ክብሩ የሀገር ነው፣ ድል የሚመጣው የብዙ ሰዎች ድምር ሲኖር ነው።›› ብለዋል።

በፌዴሬሽኑ በኩል ከበጀት አንፃር የተለያዩ ፈተናዎች ሊኖሩ እንደሚችሉ ስጋታቸውን የገለፁት አሠልጣኝ መሳይ፣ ያም ሆኖ የአሠልጣኝ ቡድን አባላት መጠናከር አለበት ባይ ናቸው። ምንም አይነት ጥቃቅን ክፍተቶች መኖር እንደሌለባቸውና የዘመኑ እግር ኳስ የሚፈልገውም ይሄንኑ እንደሆነ በመግለጫቸው ተናግረዋል።